

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## በኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን
## የአዋሽ መልካሳ ኬሚካል ፋብሪካ
## የሥራ አፈጻጸም እና የአካባቢ አያያዝ ሥርዓት
## ውጤታማነትን በተመለከተ የተከናወነ
## የአካባቢ ክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

መጋቢት 2015 ዓ.ም

አዲስ አበባ,ኢትዮጵያ

የክዋኔ ኦዲቱ ዋና ዋና ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ማጠቃለያ (Executive Summery)....i
ክፍል አንድ ....1
መግቢያ ....1
የአዋሽ መልካሳ ኬሚካል ፋብሪካ ራዕይ እና ተልዕኮ....2
የፋብሪካው ራዕይ (Vision)....2
የፋብሪካው ተልዕኮ (Mission) ....2
የፋብሪካው ስልጣንና ተግባር (Mandate and Responsibility)....2
የፋብሪካው ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል ....3
የፋብሪካው ድርጅታዊ መዋቅር (Organizational Structure) ....3
ሰንጠረዥ 1፡ የመደበኛና ካፒታል በጀት አፈፃፀም ....4
የኦዲቱ አላማ (Audit Objective) ....4
ለክዋኔ ኦዲቱ የተለየው የኦዲት አካባቢ (Audit Area)....4
የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) ....4
የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Evaluative criteria)....5
የኦዲት ወሰንና ዘዴ (Audit Scope and Methodology)....5
የኦዲት ወሰን (Audit Scope) ....5
የኦዲት ዘዴ (Audit Methodology)....6
የአዋሽ መልካሳ ኬሚካል ፋብሪካ የስራ ፍሰት (SYSTEM DESCRIPTION)....6
ክፍል ሁለት....7
የኦዲት ግኝቶች ....7
የፋብሪካው የግዥ ሂደት ህግን የተከተለ ስለመሆኑ፤ ....7
የተጫራቾች አመራረጥ እና የፐርፎርማ ግዢዎችን በተመለከተ፤ ....7
ለምርት አገልግሎት የሚውሉ የግብዓት ግዥዎችን በተመለከተ፤ ....8
የተጫራቾች አመራረጥ እና ፐርፎርማ ግዥ በተመለከተ፤....10
ለምርት አገልግሎት የሚውሉ የግብዓት ግዥዎችን በተመለከተ፡ ....10
ፋብሪካው ተመሳሳይ ገቢ ምርቶችን በራሱ ማምረቱን በተመለከተ፤....11
የፋብሪካው ንብረት አያያዝ እና ተረፈ ምርት አወጋገድ በተመለከተ፤ ....12
የፋብሪካው የግንባታ ኮንትራት አስተዳደር ውሎች ስለመፈፀማቸው እና ክትትል ስለመደረጉ፤ ....14
የፋብሪካው ፕሮጀክቶች ግንባታ በጀት እና በጊዜ ስለመፈፀሙ በተመለከተ፤ ....14
ከበጀት አንፃር....14
ከጊዜ አንፃር....15
ግንባታው የተጠናቀቀ ፕሮጀክት ርክክብን በተመለከተ፤....17
የፋብሪካው የጥገና ስርዓትን በተመለከተ፤ ....19

የገበያ መዳረሻ ጥናትን በተመለከተ፤ ....................................................................................20
የፋብሪካው ምርቶች አቅርቦትን በተመለከተ፤...............................................................21
ፋብሪካው ሊደርስበት ከሚችለው የማምረት አቅም (Attainable Design Capacity) ልክ ምርት ማምረቱን በተመለከተ፤ ......................................................21
ፋብሪካው ከሽያጭ ሊያገኘው የሚገባው ገቢ መገኘቱን በተመለከተ፤ ...............22
የፋብሪካው የምርት ጥራትን በተመለከተ፤ ..........................................................24
ፋብሪካው ከተለያዩ ድርጅቶች ጋር የገባውን የኬሚካል ምርቶች አቅርቦትን በተመለከተ፤..........................................................................................................24
የምርት ማሸጊያ ጆርካን ጥራትን በተመለከተ፤ .........................................................26
የፋብሪካው የአካባቢ፣የጤና እና ደህንነት አያያዝ ስርዓት ተግባራዊ ስለመሆኑ፤ ........................................................................................................................27
የፋብሪካው የአካባቢ አስተዳደር ደህንነት ስርዓትን በተመለከተ፤ .........................27
የጤናና ደህንነት ስርዓት ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፤.................................28
የፋብሪካው መጋዝን እና ደህንነት መሳሪያዎችን በተመለከተ፤.............................29
ለፋብሪካው ምርት ግብዓቶች የሚሆኑ መጋዘኖችን በተመለከተ፤..........................29
የአደጋ ጊዜ ጠቃሚ መሣሪያዎችን በተመለከተ፤ ..................................................30
የፋብሪካው ምርት በሚጓጓዝበት ወቅት ስለሚያደርገው የደህንነት ጥንቃቄ፤.........31
ክፍል ሦስት .............................................................................................................33
መደምደሚያ .............................................................................................................33
ክፍል አራት..............................................................................................................36
የማሻሻያ ሃሳቦች.......................................................................................................36
አባሪ አንድ ................................................Error! Bookmark not defined.
የአዋሽ መልካሳ ኬሚካል ፋብሪካ ድርጅታዊ መዋቅር..... Error! Bookmark not defined.
አባሪ ሁለት .................................................................................... ii
የመመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria) ............................................. ii
አባሪ ሶስት...................................................................................... vi
የአዋሽ መልካሳ ኬሚካል ፋብሪካ የአሰራር ስርዓት መግለጫ .................. vi
አባሪ አራት ..................................................................................... vii
ፋብሪካው የሚፈለገው ምርት ስለመገኘቱ፤ ............................................ vii

## የክዋኔ ኦዲቱ ዋና ዋና ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ማጠቃለያ (Executive Summery)

የኬሚካል ኢንዱስትሪ ሴክተር በጣም ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው እና በሰው ልጆች አኗኗር ውስጥ እጅግ አስፈለጊ የሆኑ ምርቶችን በመፍጠር /በማልማት የሚታወቅ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ትልቁ ዘርፍ ሲሆን ሴክተሩ ሠፊ ብዛት ያላቸውን ጥሬ ዕቃዎች ከአካባቢ አየርና ከማእድን እንዲሁም ከተፈጥሮ ዘይት የሚጠቀም ነው፡፡ከዚህ ሴክተር የሚገኙ በርካታ ውጤቶች በቀጥታ ለፍጆታ ዕቃነት የሚውሉ እና ቀሪዎቹና ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው ደግሞ ለሌሎች ምርቶች ማምረቻነት የሚዉሉ ናቸው፡፡

እንዲሁም ሀገራችን ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ በሽግግር ሂደት ላይ በመሆኗ ከውጭ ሀገር የሚገቡ ወይም በሀገር ውስጥ የሚመረቱ የኢንዱስትሪ ኬሚካሎች መጠን እያደገ በመምጣቱ የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባት፣በማጓጓዝ፣ በማከማቸት፤ በማምርትና በመጠቀም ሂደት ከአያያዝ ጉድለት በሰው፤በእንስሳት ጤና እና በአካባቢ ደህንነት ላይ ሊከሰቱ የሚችሉ ጉዳቶችን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል፡፡

የአካባቢ ክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ በኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን የአዋሽ መልካሳ ኬሚካል ፋብሪካ የሥራ አፈጻጸም እና የአካባቢ አያያዝ ሥርዓት ውጤታማነትን በተመለከተ የሚታዩ የአሠራር ክፍተቶችን እና የችግሮቹን መንስኤ በመለየት የማሻሻያ ሀሳቦችን በማቅረብ ተጠያቂነት እንዲጠናከር ለማድረግ ነው፡፡

የአካባቢ ክዋኔ ኦዲቱ የተመረጡት የትኩረት አቅጣጫዎች፡ በፋብሪካው የሚከናወኑ ግዥዎች የመንግስት ግዥ ሕጎችን የተከተሉና የንብረት አሰተዳደር ስርዓት ውጤታማ መሆኑን መገምገም፤ በፋብሪካው የሚከናወኑ ግንባታዎች የኮንትራት ውል አስተዳደር ውጤታማነትን መገምገም፤ ፋብሪካው የምርትና የማምረት ብቃት (Operation and Process Efficiency) ሂደትን መገምገም እና ፋብሪካው የአካባቢ አያያዝ ስርዓት ውጤታማነትን መገምገም የሚሉ ናቸው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው በአዋሽ መልካሳ ኬሚካል ፋብሪካ እና በኦሮሚያ ክልል (የምስራቅ ሸዋ አካባቢ፤ደንና አየር ንብረት ለውጥ ፅ/ቤት እና የአዋሽ መልካሳ ከተማ ከንቲባ ፅ/ቤት) ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ጋር ቃለ መጠይቅ በማድረግ እና ቼክሊስት በመሙላት ተያያዥነት ያላቸውን ማስረጃዎች በመከለስ፣ በአካል በመገኘት እና መረጃዎችን በመተንተን ነው፡፡

DRAFT

የክዋኔ ኦዲቱ የተከናወነው በአለም አቀፉ እና በኢትዮጵያ የክዋኔ የኦዲት ስታንዳርድ እንዲሁም ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ነው፡፡ ዝርዝር ኦዲቱ የሸፈነው ከ2012 እስከ 2015ዓ.ም የአንደኛው ሩብ ዓመት ድረስ ያሉ የሥራ ክንውኖችን ነው፡፡

በኦዲቱ ወቅት በኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን የአዋሽ መልካሳ ኬሚካል ፋብሪካ የሥራ አፈጻጸም እና የአካባቢ አያያዝ ሥርዓት ውጤታማነትን በተመለከተ ያለው አፈፃፀም ላይ የሚከተሉት ክፍተቶች ታይተዋል፡-

- የፋብሪካው የፕሪፎርማ ግዥዎች የመንግስት ግዥ መመሪያን እና የኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን የግዥ መመሪያ ቁጥር 07/2012 ያልተከተሉ መሆኑ፤ እንዲሁም ለምርት አገልግሎት የሚውሉ የግብዓት ግዥዎችን ሲፈፅም ዝርዝር የግዥ ዕቅድ የሌለውና በተፈለገው ጊዜ፣መጠን፣ጥራት እና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ ያልተከናወኑ ናቸው፡፡
- የፋብሪካው ነባር ፋብሪካዎችን መልሶ የማቋቋም እና የሃይድሮጅን ፐርኦክሳይድ ፋብሪካ የግንባታ ፕሮጀክቶች ኮንትራት ውሉ ላይ በተቀመጠው መስፈርት /Specification/ እና በውል ሰነዱ የጥራት ስታንዳርድ መሰረት በተያዘላቸው በጀት እና ጊዜ ተገንብተው ወደ ምርት ማምረት ሂደት አልገቡም፡፡ በዚህም ምክንያት የሃይድሮጅን ፐርኦክሳይድ ፋብሪካ የግንባታ ፕሮጀክት ውል ከተገባው የ86,243,291.06 (የሰማኒያ ስድስት ሚሊዮን ሁለት መቶ አርባ ሦስት ሺህ ሁለት መቶ ዘጠና አንድ ብር ከስድስት ሳንቲም) ወይም 60.68% ጭማሪ ወጪ ተዳርጓል፡፡
- ፋብሪካው ለሚያመርታቸው የኬሚካል ምርቶች በየወቅቱ የደሰሳ ጥናት በማድረግ የገበያ መዳረሻዎችን (በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር) ያላሰፋ በመሆኑ ከገበያ ድርሻው ሊያገኝ የሚገባውን ገቢ እንዲያጣ አድርጓል፡፡
- ፋብሪካው ምርታማነቱን በማሳደግ የአልሙኒየም ሰልፌት፣ ሰልፈሪክ አሲድ እና ሃይድሮጅን ፐር ኦክሳይድ ኬሚካል ምርቶች በሶስት አመት (ከ2012-2014 ዓ.ም) ሊደርስበት ከሚችለው የማምረት አቅም (Attainable Design Capacity) ልክ (30,308 ቶን) ባለማምረቱ ብር 277,996,009.60 ማግኘት የነበረበትን ገቢ እንዲያጣ እንዲሁም ከተለያዩ ድርጅቶች ጋር የገባውን የኬሚካል ምርቶች አቅርቦት በገባው የውሉ ኮንትራት መሰረት በወቅቱ መፈፀም እንዳይችል አድርጓል ፋብሪካው ለሚያመርታቸው ምርቶች ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት የጥራት ማረጋገጫ በማግኘት የምርት ጥራት መረጃ በምርት ማሸጊያዎቹ ላይ እንዲለጠፍ አያደርግም፡፡ ይህም በ2017 ዓ.ም በምስራቅ አፍሪካ ካሉ ኬሚካል ፋብሪካዎች ግንባር ቀደም በመሆን ተወዳዳሪ ለመሆን ፋብሪካው ከያዘው ራዕይ አንፃር ሊያሳካ የሚያስችል አይደለም፡፡

☞ ፋብሪካው የአከባቢ አስተዳደር ስርዓትን በመዘርጋት የደረቅ እና የፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ እንዲሁም የአየር ብክለት መከላከል ስራዎችን በአግባቡ አልሰራም፤ የጤና እና ደህንነት ስርዓት በመዘርጋት ለሠራተኞቹ የአደጋ መከላከያ ትጥቆችና አልባሳትን በወቅቱና በተፈለገ ጊዜ በማቅረብ በሥራ ላይ የሚደርሱ ጉዳቶችን ለመከላከል የሚያስችል ደህንነቱ የተጠበቀ የሥራ አካባቢን አልፈጠረም፡፡

**ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ ከላይ የተመለከቱት ግኝቶች መፍትሄ ሊሆን የሚችሉ የማሻሻያ ሃሳቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡-**

☞ ፋብሪካው የሚፈጽማቸው የፐርፎርማ ግዥዎች የመንግስት ግዥ መመሪያን እና የኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን የግዥ መመሪያ ቁጥር 07/2012 የተከተሉ እንዲሆኑ እንዲሁም ለምርት አገልግሎት የሚውሉ የግብዓት ግዥዎችን ሲፈፅም በዕቅድ ሊመራና በተፈለገው ጊዜ፣ መጠን፣ ጥራት እና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ እንዲከናወን ሊያደርግ ይገባል፡፡

☞ ፋብሪካው ያለበትን የመከታተል ሃላፊነት ትኩረት ሰጥቶ በመፈፀም ነባር ፋብሪካዎችን መልሶ የማቋቋም የግንባታ ፕሮጀክቶች ኮንትራት ውሉ ላይ በተቀመጠው መስፈርት /Specification/ እና በውል ሰነዱ የጥራት ስታንዳርድ መሰረት በተያዘላቸው በጀት እና ጊዜ ገንብተው ወደ ምርት ማምረት ሂደት ማስገባት አለበት፤

☞ ፋብሪካው የገበያ መዳረሻ ጥናት ለምርት ሽያጭ አፈፃፀም ያለውን አስተዋፅኦ በአግባቡ በመረዳት እና ለሚያመርታቸው የኬሚካል ምርቶች በየወቅቱ የደሰሳ ጥናት በማድረግ የገበያ መዳረሻዎችን (በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር) ሊያሰፋና ከገበያ ድርሻው ሊያገኝ የሚገባውን ገቢ ሊያሳድግ ይገባል፡፡

☞ ፋብሪካው የፋብሪካው መሳሪያዎች ቴክኒካል ችግሮች በአስቸኳይ እንዲፈቱ በማድረግ እና ዘመናዊ የማምረት አሰራሮችን በመተግበር ሊደርስበት ከሚችለው የማምረት አቅም (Attainable Design Capacity) ልክ በማምረት ምርታማነቱን ሊያሳድግ እና ከተለያዩ ድርጅቶች ጋር የሚገባውን የኬሚካል ምርቶች አቅርቦት በሚገባው የውሉ ኮንትራት መሰረት በወቅቱ መፈፀም አለበት፡፡

☞ ፋብሪካው ለአካባቢ አስተዳደር እና ጤና ደህንነት ለመጠበቅ የሚያስችሉ ስርዓቶች ተገቢውን ትኩረት በመስጠት የአካባቢ አስተዳደር ስርዓትን በመዘርጋት የደረቅ እና የፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ እንዲሁም የአየር ብክለት መከላከል ስራዎችን በአግባቡ ሊሰራ በተጨማሪም የጤና እና ደህንነት ስርዓት በመዘርጋት ለሠራተኞቹ የአደጋ መከላከያ ትጥቆችና አልባሳትን በወቅቱና በተፈለገ ጊዜ በማቅረብ በሥራ ላይ የሚደርሱ ጉዳቶችን ለመከላከል የሚያስችል ደህንነቱ የተጠበቀ የሥራ አካባቢን መፍጠር አለበት፡፡
የሚሉት ይገኙበታል፡፡

DRAFT

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. የኬሚካል ኢንዱስትሪ ሴክተር በጣም ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው እና በሰው ልጆች አኗኗር ውስጥ እጅግ አስፈለጊ የሆኑ ምርቶችን በመፍጠር /በማልማት የሚታወቅ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ትልቁ ዘርፍ ሲሆን ሴክተሩ ሠፊ ብዛት ያላቸውን ጥሬ ዕቃዎች ከአካባቢ አየርና ከማእድን እንዲሁም ከተፈጥሮ ዘይት የሚጠቀም ነው፡፡ከዚህ ሴክተር የሚገኙ በርካታ ውጤቶች በቀጥታ ለፍጆታ ዕቃነት የሚውሉ እና ቀሪዎቹና ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው ደግሞ ለሌሎች ምርቶች ማምረቻነት የሚዉሉ ናቸው፡፡
2. እንደ አዋሽ መልካሳ ኬሚካል ፋብሪካ ያሉ የሀገራችን የኬሚካል ኢንዱስትሪ ዘርፍ ሲቃኝ ገና በማደግ ላይ የሚገኝና የሚያበረክተው አስተዋፅኦ እጅግ ዝቅተኛ ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት የሀገራችን የኬሚካል ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ውስጥ ስትራቴጂክ ሴክተር ተብለው ከተለዩት መካከል አንዱ ለመሆን የቻለ ሲሆን ይህን መሠረት በማድረግም መንግሥት የኬሚካል ኢንዱስትሪዎችን ልማት ለመቆጣጠር በማሰብ በ21.7 ቢሊዮን ብር ኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽንን ያቋቋመ ሲሆን በሥሩም ጥቂት የኬሚካል ዉጤቶችን የሚያመርቱ ፋብሪካዎችን እና ፕሮጀክቶችን እያንቀሳቀሰ ይገኛል፡፡
3. እንዲሁም ሀገራችን ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ በሽግግር ሂደት ላይ በመሆኗ ከውጭ ሀገር የሚገቡ ወይም በሀገር ውስጥ የሚመረቱ የኢንዱስትሪ ኬሚካሎች መጠን እያደገ በመምጣቱ የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባት፣በማጓጓዝ፣ በማከማቸት፤ በማምረትና በመጠቀም ሂደት ከአያያዝ ጉድለት በሰው፤በእንስሳት ጤና እና በአካባቢ ደህንነት ላይ ሊከሰቱ የሚችሉ ጉዳቶችን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል፡፡
4. በዚሁ መሰረት የአዋሽ መልካሳ ኬሚካል ፋብሪካ በሐምሌ ወር 1987 ዓ.ም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 257/1987 ተቋቋመ፤ የመንግስት ልማት ድርጅቶችን በከፊልም ሆነ ሙሉ ለሙሉ ወደግል ይዞታነት ለማዛወር በወጣው አዋጅ ቁጥር 146/1990 መሠረት እ.ኤ.አ ከጥር 1 ቀን 2000 ጀምሮ አዋሽ መልካሳ አሉሚኒያም ሰልፌትና ሰልፈሪክ አሲድ አክስዮን ማህበር በመባል እንደገና በመቋቋም ሲሠራ ከቆየ በኋላ በመስከረም ወር 2009 ዓ.ም በሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር 416/2009 ውሳኔ መሠረት ድርጅቱ ከኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን ጋር በመዋሃድ አዲሱን አዋሽ መልካሳ ኬሚካል ፋብሪካ የሚለውን ስያሜ አገኘ፡፡

DRAFT

5. ፋብሪካው ከምሥረታ ጊዜው ጀምሮ ለ13 ተከታታይ ዓመታት በኪሣራ ሲንቀሳቀስ ቆይቶ ችግሮችን ለመቅረፍ በተከተላቸው አቅጣጫዎች ከ2001 ዓ.ም ጀምሮ እስካሁን ድረስ ትርፋማ መሆን የቻለ ቢሆንም ባሉበት ቴክኒካል ችግሮች እና የገበያ ችግር ሳቢያ ከአቅም በታች እንዲሠራ በመገደዱ ምክንያት በቀጣይነት ትርፋማነቱን ማሳደግ ያልቻለ ድርጅት ነው፡፡

**የአዋሽ መልካሳ ኬሚካል ፋብሪካ ራዕይ እና ተልዕኮ**

**የፋብሪካው ራዕይ** (Vision)

6. በ2017 በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር (እ.ኢ..አ) ዘመናዊ የአመራረት ቴክኖሎጂን በመጠቀም አሁን ያሉትን ኬሚካሎች ጨምሮ ሌሎች ለከባድ ኢንዱስትሪ መሠረት የሚጥሉ እና የሀገራችንን ዕድገት የሚያፋጥኑ አዳዲስ ኬሚካሎችን የሚያመርት በሀገራችንና በምስራቅ አፍሪካ ቀዳሚና ተመራጭ የኬሚካል ኢንዱስትሪ መሆን ነው፡፡

**የፋብሪካው ተልዕኮ** (Mission)

7. ዓለም አቀፍ የጥራት ደረጃን ያሟሉ አሉሚኒየም ሰልፌት፣ሰልፈሪክ አሲድ እና ሃይድሮጅን ፐርኦክሳይድ ኬሚካሎችን ከአካባቢ ብክለት በፀዳ መልኩ በአነስተኛ ዋጋ አምርቶ በተወዳዳሪ ዋጋ ለገበያ በማቅረብ የደንበኞችን ፍላጎት ማርካትና ትርፋማ መሆን እንዲሁም ከውጭ ሀገር የሚገቡትን ተመሣሣይ ምርቶች በማስቀረት የሀገሪቱን የውጭ ምንዛሪ ማዳንና ከሀገሪቱ ፍጆታ የሚተርፈውን ምርት ለውጭ ሀገር ገበያ የማቅረብ ራዕይ ያለው ፋብሪካ ነው፡፡

**የፋብሪካው ስልጣንና ተግባር** (Mandate and Responsibility)

8. በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 416/2009 ፋብሪካው ሲቋቋም በተሰጠው ሕጋዊ ሰውነት መሠረት አሉሚኒየም ሰልፌት፣ሰልፈሪክ አሲድ፣ሃይድሮጅን ፐርኦክሳይድ እንደ አስፈላጊነቱ ሲንግል ሱፐርፎስፌት፣ ሶዲየም ሳልፌት፣ ማግኒዥየም ሳልፌት፣አሊየም እና ሌሎች ተመሳሳይ ምርቶች እያመረተ ለገበያ ማቅረብ ነው፡፡
9. በዚህ ሥራ ሂደትም ለባለድርሻ አካላትና ለመንግሥት በሕግ የተሰጡትን ግዴታዎችንና ክፍያዎችን መፈፀም ከበላይ አካል የሚተላለፉትን ፖሊሲዎችንና መመሪያዎችን መፈፀምና ማስፈፀም ነው፡፡

10.በተጨማሪም የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባት፣በማጓጓዝ፣ በማከማቸት፤ በማምርትና በመጠቀም ሂደት ከአያያዝ ጉድለት በሰው፤በእንስሳት ጤና እና በአካባቢ ደህንነት ላይ ሊከሰቱ የሚችሉ ጉዳቶችን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ የኢንዱስትሪ ኬሚካሎች ምዝገባና አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1075/2011 ታዉጇል፡፡

**የፋብሪካው ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል**

**የፋብሪካው ድርጅታዊ መዋቅር** (Organizational Structure)

11.አዋሽ መልካሳ ኬሚካል ፋብሪካ ተጠሪነቱ ለኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን ሲሆን በዋና ሥራ አስኪያጅ የሚመራ ነው፡፡ በዋና ሥራ አስኪያጅ ስር ም/ሥራ አስኪያጅ እና የውስጥ ኦዲት አገልግሎትን ጨምሮ ስድስት መምሪያዎች እና በሰባት ቡድን ተዋቅሯል፡፡ **(ዝርዝሩ በአባሪ 1 ተያይዟል)**

**የፋብሪካው የሰው ኃይል** (Human Resource)

12.ለፋብሪካው በመዋቅር የተፈቀደ የስራ መደብ 410 ሲሆን እስከ ግንቦት 2014 ድረስ 72 ሴቶች (22.43%) እና 249 ወንዶች (77.57%) በድምሩ 321 ቋሚ ሰራተኞች አሉት፡፡ የሰራተኞች ፕሮፋይል በትምህርት ደረጃ ሲታይ በኤም.ኤስ.ሲ/ኤም.ኤ ደረጃ ያሉ 16 (4.98%)፣ የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው 87 (27.1%)፣ ኮሌጅ ዲፕሎማ 99 (30.84%)፣ እንዲሁም የቀለም ትምህርት ያላቸው ሰራተኞች 119 (37.07%) ነው፡፡

**የፋብሪካው የፋይናንስ ምንጭ** (Source of Finance)

13.የአዋሽ መልካሳ ኬሚካል ፋብሪካ በአዋጅ የተሰጠውን ተግባር ለማከናወን መደበኛ እና ካፒታል በጀት ከሚያመርታቸው የምርቶች ሽያጭ ከሚሰበስበው ገቢ የሚመድብለት ሲሆን፡ ከ2012-2014 ዓ.ም ድረስ የተመደበለት በጀትና የወጣው ወጪ በሚከተለው ሰንጠረዥ ተመልክቷል፡፡

DRAFT

ሰንጠረዥ 1፡ **የመደበኛና ካፒታል በጀት አፈፃፀም**

| ዓመት | የተመደበ በጀት | | | ጥቅም ላይ የዋለ በጀት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | መደበኛ | ካፒታል | ድምር | መደበኛ | ካፒታል | ድምር | በመቶኛ % |
| 2012 | 132,216,000 | 237,386,000 | 369,602,000 | 61,217,000 | 1,310,000 | 62,527,000 | 17 |
| 2013 | 153,218,000 | 210,245,000 | 363,463,000 | 53,874,000 | 751,000 | 54,625,000 | 15 |
| 2014 | 297,477,000 | 217,881 | 515,358,000 | 112,875,000 | 590,000 | 113,465,000 | 22 |

**የኦዲቱ አላማ** (Audit Objective)

14.የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ በኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን የአዋሽ መልካሳ ኬሚካል ፋብሪካ የሥራ አፈጻጸም እና የአካባቢ አያያዝ ሥርዓት ውጤታማነትን በተመለከተ ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ፣ ውጤታማ እና ከብክለት የጸዳ የአካባቢ አያያዝ ስርዓት የሚከተል መሆኑን በማረጋገጥ በሥራው ዙሪያ የሚታዩ የአሠራር ችግሮች ወይም ክፍተቶች ካሉ ችግሮቹን እና መንስኤያቸውን በመለየት ችግሮቹን ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሀሳቦችን ለማቅረብ ነው፡፡

**ለክዋኔ ኦዲቱ የተለየው የኦዲት አካባቢ** (Audit Area)

15.ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ፣ በኬሚካል እንዱስትሪ ኮርፖሬሽን የአዋሽ መልካሳ ኬሚካል ፋብሪካ የሥራ አፈጻጸም እና የአካባቢ አያያዝ ሥርዓት ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ እየተከናወነ መሆኑን መገምገም" የሚል ነው፡፡

**የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች** (Audit Issues)

16.ከላይ በተመረጠው የኦዲት አካባቢ ሥር አራት ዋና የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች /Audit Issues/ የተለየ ሲሆን እነሱም ፡-

1. በፋብሪካው የሚከናወኑ ግዥዎች የመንግስት ግዥ ሕጎችን የተከተሉና የንብረት አሰተዳደር ስርዓት ውጤታማ መሆኑን መገምገም፤
2. በፋብሪካው የሚከናወኑ ግንባታዎች የኮንትራት ውል አስተዳደር ውጤታማነትን መገምገም፤
3. ፋብሪካው የምርትና የማምረት ብቃት (Operation and Process Efficiency) ሂደትን መገምገም፤

DRAFT

4. ፋብሪካው የአካባቢ አያያዝ ስርዓት ውጤታማነትን መገምገም፣የሚሉ ናቸው፡፡

**የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Evaluative criteria)**

17.ከላይ የተጠቀሱትን አራት ዋና ዋና የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎችን ለመመዘን የሚረዱ 21 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ እነዚህን የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ለማዘጋጀት መሰረት የሆኑት የፌዴራል መንግስት አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 1067/2010፣ የኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 280/2005፣ አዋሽ መልካሳ ኬሚካል ፋብሪካ በሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር 416/2009 ከኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን ጋር የተዋሀደበት፣የድርጅቱ ስትራቴጂክ ዕቅድ (ከ2013 -2017)፣የኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን የሽያጭና ማከፋፈያ መመሪያ ቁጥር 4/2012፣ የአዋሽ መልካሳ ኬሚካል ፋብሪካ ከ2012 እስከ 2014 በጀት ዓመታት ያሉ የዕቅድ አፋፃፀም ሪፖርቶች፣ የድርጅቱ ወጪ እና ገቢ ደብዳቤዎች፣ የድርጅቱ የማኔጅመንት ቃለ-ጉባኤዎች (ከ2012-2014)፣ የኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን የግዥ መመሪያ ቁጥር 07/2012፣የአካባቢ አስተዳደር ደህንነት ስርዓት (Environmental Management System) ሰነድ፣የጥራት ማኔጅመንት ስርዓት (Quality Management System)ሰነድ፣የጤናና ደህንንት ስርዓት (Occupational Safety and Health Management) ሰነድ በማካተት የተዘጋጀ ነው፡፡ የተዘጋጁት የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ለኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ተልከው የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች አስተያየት እንዲሰጡባቸው ተደርጓል፡፡ (የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶቹ በአባሪ 2 ተያይዘዋል፡፡)

## የኦዲት ወሰንና ዘዴ (Audit Scope and Methodology)

### የኦዲት ወሰን (Audit Scope)

18.ኦዲቱ የተከናወነው በመንግሥት መ/ቤቶች ላይ የክዋኔ ኦዲትን ለማካሄድ ለፌደራል ዋና ኦዲተር በአዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ሥልጣንና በአለማቀፍ የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች(International Performance Audit Standards) መሰረት ነው፡፡ የክዋኔ ኦዲቱ የሸፈነው ከ2012 እስከ 2015 1ኛ ሩብ በጀት ዓመት ድረስ ያለውን የአዋሽ መልካሳ ኬሚካል ፋብሪካ ሥራ አፈጻጸም እና የአካባቢ አያያዝ ሥርዓት የሥራ ክንውኖች ነዉ፡፡

DRAFT

**የኦዲት ዘዴ (Audit Methodology)**

19. ዝርዝር ኦዲቱ በዋነኛነት በአዋሽ መልካሳ ኬሚካል ፋብሪካ የተከናወነ ሲሆን በሁለት የሚመለከታቸው (በኦሮሚያ ክልል) የምስራቅ ሸዋ አካባቢ፤ደንና አየር ንብረት ለውጥ ፅ/ቤት፤ የአዋሽ መልካሳ ከተማ ከንቲባ ፅ/ቤት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ጋር ቃለ መጠይቅ በማድረግ እና ቼክሊስት በመሙላት ተያያዥነት ያላቸውን ማስረጃዎች በመከለስ፣ በአካል በመገኘት እና መረጃዎችን በመተንተን ነው፡፡

**የአዋሽ መልካሳ ኬሚካል ፋብሪካ የስራ ፍሰት (SYSTEM DESCRIPTION)**

20. የአዋሽ መልካሳ ኬሚካል ፋብሪካ ከኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬት ስትራቴጂ በመነሳት የተቀናጀ እቅድ በማቀድ፤አሉሚኒየም ሰልፌት፣ሰልፈሪክ አሲድ እና ሃይድሮጅን ፐርኦክሳይድ ኬሚካሎችን ከአካባቢ ብክለት በፀዳ መልኩ በአነስተኛ ዋጋ አምርቶ በተወዳዳሪ ዋጋ ለገበያ በማቅረብ የደንበኞችን ፍላጎት የማርካትና ትርፋማ የመሆን ሥራ ይሰራል፡፡ (የስራ ፍሰቱን የሚያሳይ ዝርዝር **በአባሪ 3 ተያይዟል፡፡**)

DRAFT

# ክፍል ሁለት

## የኦዲት ግኝቶች

### የፋብሪካው የግዥ ሂደት ህግን የተከተለ ስለመሆኑ፤

21.ፋብሪካው መልሶ የሚያቋቁማቸው እና የሚያስገነባቸው የኬሚካል ፋብሪካ ፕሮጀክቶች አለም አቀፍ የግዥ ሕጎችንና የመንግስት ግዥ ህግና መመሪያ ሂደትን የተከተሉ እንዲሆኑ ሊያደርግ እንዲሁም ለምርት አገልግሎት የሚውሉ የግብዓት ግዥዎችን ሲፈፅም በዕቅድ ሊመራና በተፈለገው ጊዜ፣ መጠን፣ ጥራት እና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ ሊፈጽም ይገባል፡፡

22.ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-

- <u>የተጫራቾች አመራረጥ እና የፐርፎርማ ግዢዎችን በተመለከተ፤</u>

  - የኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን የግዥ መመሪያ ቁጥር 07/2012 ንዑስ አንቀጽ 6.6.1 (ሐ) መሠረት ዕቃዎች/ አገልግሎቶች በፐርፎርማ መግዛት የሚቻለው በተወዳዳሪነት ሊቀርቡ የሚችሉ እጅግ ቢያንስ ሦስት አቅራቢዎች መኖራቸው ሲረጋገጥ እና ንዑስ አንቀጽ 6.6.7 መሠረት በአንድ ፐርፎርማ የሚከናውን የዕቃ/አገልግሎት ግዥ አጠቃላይ ዋጋ ከብር 250,000 (ሁለት መቶ ሃምሳ ሺህ ብር) መብለጥ እንደሌለበት የሚደነግግ ቢሆንም፤

    - ☞ ፋብሪካው መልሶ የሚያቋቁማቸው የአሉሚኒየም ሰልፌት እና ሰልፈሪክ አሲድ ፕሮጀክቶች 2 ጊዜ አለም አቀፍ ጨረታ ያወጣ ሲሆን፤ በውስን ጨረታ አራት ድርጅቶችን በመጋበዝ እና በማወዳደር ከዚህ ቀደም የሃይድሮጅን ፐርኦክሳይድ ኬሚካል ፋብሪካን ግንባታ ስራን ውል በገባው ጊዜና በጀት ያላጠናቀቀ እና መልካም የሥራ አፈፃፀም ለሌለው ለኑበርግ ኢንጂነሪንግ (NUBERG ENGINEERING LTD) የተሰጠ መሆኑ፤
    - ☞ ፋብሪካው ከተለያዩ ድርጅቶች በፐርፎርማ የሚገዛቸው ግዥዎች የመንግስትን የግዥ መመሪያ እና የኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን የግዥ መመሪያ ቁጥር 07/2012 መሰረት ያልተከናወነ መሆኑ፤

DRAFT

ለአብነት፡- የሃላ ፎርክ-ሊፍት ሙሉ የኢንጂን እድሳትና ጥገና ሥራ በፕርፎርማ ከሚፈቀደው ግዥ መጠን 250ሺ በላይ በሆነ ዋጋ በብር 326,137.50 እና የሰሌዳ ቁጥር 3-ኢት-32787፣የሞዴል ቁጥር-k77,serial Number-L200 ሚትሱቢሺ ተሽከሪካሪ የኢንጂን እድሳትና የጥገና ሥራ በብር 1,041,214.37 ግዥ የፈፀመ መሆኑ፤

- <u>ለምርት አገልግሎት የሚውሉ የግብዓት ግዥዎችን በተመለከተ፤</u>

- ፋብሪካው ለምርት አገልግሎት የሚውሉ የግብዓት ዝርዝር የግዥ ዕቅድ አፈፃፀም ከ2012 ዓ.ም እስከ 2015 ዓ.ም አንደኛ ሩብ ዓመት ማስረጃ በኦዲት ቡድኑ ተጠይቆ ያልቀረበ መሆኑ፤
- ፋብሪካው የግብዓት ግዥዎችን በተፈለገው ጊዜ፣መጠን እና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ የማይፈፅም መሆኑ፤ለአብነት፡-
  - ☞ ለሃይድሮጅን ፐርኦክሳይድ ምርት የሚያገለግሉ እ.ኤ.አ 26/07/2016 ተገዝተው የገቡ ኬሚካሎች ፓላዲሂም ካታሊስት (Palladium Catalyst) 50 ኪሎግራም በብር 1,102,012.25 ፤አክቲቬትድ አሉሚና (Activated Alumina) 15,400 ኪሎግራም በብር 2,996,228.31፤Ethyl Antha Quinone 1,600 ኪሎግራም በብር 245,739.85 እና Tri-Octyl Phosphate 360 ኪሎግራም በብር 183,520.31 በጠቅላላ **17,410** ኪሎግራም በብር 4,527,500.72 እንዲሁም እ.ኤ.አ 28/03/2022 ተገዝቶ የገቡ ኬሚካሎች ፓላዲሂም ካታሊስት (Palladium Catalyst) 50 ኪሎግራም፤አክቲቬትድ አሉሚና (Activated Alumina) 12,000 ኪሎግራም እና Ethyl Antha Quinone 875 ኪሎግራም በጠቅላላ **12,925** ኪሎግራም በብር 14,522,356.45 በአጠቃላይ 30,335 ኪሎግራም ብር 19,049,857.17 ወጪ የወጣባቸው ኬሚካሎች ውስጥ 3460 ኪሎግራም ብር 3,425,488.47 መጠን ያላቸው ኬሚካሎች የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈባቸው/Expired/ መሆኑ፤

| የኬሚካል አይነት | እ.ኤ.አ 26/07/2016 ተገዝተው የገቡ | | እ.ኤ.አ 28/03/2022 ተገዝተው የገቡ | |
|---|---|---|---|---|
| | መጠን (በኪሎ ግራም) | ዋጋ (በብር) | መጠን (በኪሎ ግራም) | ዋጋ (በብር) |
| ፓላዲሂም ካታሊስት (Palladium Catalyst) | 50 | 1,102,012.25 | 50 | 14,522,356.45 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| **አክቲቬትድ አሉሚና** (Activated Alumina) | 15,400 | 2,996,228.31 | 12,000 | |
| Ethyl Antha Quinone | 1,600 | 245,739.85 | 875 | |
| Tri-Octyl Phosphate | 360 | 183,520.31 | | |
| **ጠቅላላ ድምር** | **17,410** | 4,527,500.72 | **12,925** | 19,049,857.17 |

ሰንጠረዥ 2፡ የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈባቸው /Expired/ ያደረጉ እና ያላደረጉ ኬሚካሎች

☞ በ2012 በጀት ዓመት ፋብሪካው የአልሙኒየም ሰልፌት ጥሬ ዕቃ ካኦሊን እና አሉሚኒየም ሃይድሮ ኦክሳይድ ጥሬ እቃ በተፈለገው ጊዜ እና መጠን ተገዝቶ ባለመቅረቡ መመረት የነበረበት **4978** ቶን አልሙኒየም ሰልፌት ሳይመረት የቀረ መሆኑ፣

☞ በ2013 ዓ.ም በሄራልድ ጋዜጣ የጨረታ ማስታወቂያ ቁጥር (invitation to Bid Tender No) CIC-AMCF-SUL-AH-HPCH-001/2013 E.B.Y.ለ3314 ቶን አሉሚኒየም ሃይድሮ ኦክሳይድ እና ለ684 ቶን ሰልፈር(ድኝ) ግዥ ፋይናንሻል የጨረታ ሰነድ ተጫራቾች በሌሉበት እና ቀኑን ባልጠበቀ መልኩ በመከፈቱ ጨረታው እንዲሰረዝ በመደረጉ ፋብሪካው በ2014 በጀት ዓመት 11 ወራት ምርት እንዳይመረት ምክንያት መሆኑ፤

☞ እንዲሁም በ2013 በጀት ዓመት 800 ቶን የአሉሚኒየም ሃይድሮ ኦክሳይድ እና 1440 ቶን ድኝ/ሰልፈሪክ አሲድ/ እ.ኤ.አ ጃንዋሪ 25/2021 ላይ ኤሊሲ (LC) ተከፍቶ የግዥ ሂደቱ የተጀመረ ቢሆንም ጥሬ ዕቃዎች በተፈለገው ጊዜ ያልተጫነ መሆኑ፣

☞ በ2014 በጀት ዓመት ለአሉሚኒየም ሰልፌት ምርት ዋና ጥሬ ዕቃ የሆኑት ከሀገር ውስጥ ካኦሊን እና ከውጭ ሀገር አሉሚኒያም ሃይድሮኦክሳይድ የግዥ ሂደቱ በተፈለገው ጊዜ፣መጠን እና ወጪ ተጠናቆ ፋብሪካ ባለመድረሱ ለ11 ወራት በላይ ምርት ያልተመረተ መሆኑ፤

☞ በ2014 በጀት ዓመት የሰልፈሪክ አሲድ ጀሪካን ብዛት 52,000 የሀይድሮጅን ፐርኦክሳይድ ጀሪካን ብዛት 40,000 በጠቅላላ 92,000 ሺ ጀሪካን ለማቅረብ ጨረታውን ያሸነፈው AB ፕላስት ድርጅት ባሸነፈው ዋጋ ላይ 30% ጭማሪ በማድረግ ያቀረበ መሆኑ፤

DRAFT

23.ስለጉዳዩ የፋብሪካው የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ፣በረቂቅ ሪፖርት እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት መልስ፡-

- የተጫራቾች አመራረጥ እና ፐርፎርማ ግዥ በተመለከተ፣

➢ ነባሮቹን ፋብሪካ መልሶ ማደስ ፕሮጀክት ሂደት ፋብሪካው ለሁለት ጊዜያት ያህል በጋዜጣ ጨረታ ያሳወጀ ቢሆንም የጨረታ ሰነድ የገዙ 13 ድርጅቶች በጨረታ መዝጊያ ቀን ባለመገኘታቸው ከቀረቡት ሶስቱ ድርጅቶች አንደኛው Bidbond ባለማቅረቡ ከጨረታው እንዲወጣ መደረጉን ሁለቱ ለቴክኒክ ምዘና የቀረቡ መሆኑና ከሁለቱ አንደኛው ብቻ የቴክኒክ መስፈርቱን በደንቡ መሰረት ያሟላ ስለሆነ መመረጡ፣የNuberg Engineering LTD ፕሮጀክት አፈጻጸም በተመለከተ በዋናነት በክፍተት የታየው አንድ ኮምፕሬስር ሲሆን ድርጅቱ ኮምፕሬሰሩን እንዲተካ ከማድረጉ በተጨማሪ ኮምፕሬሰሩ ኮሚሺኒንግ እስከሚደረግ ድረስ ተመጣጣኝ 60,000 ዶላር እንዲያሲዝ የተደረገ መሆኑን፣

➢ የሁለቱ መኪኖች ጥገና ግዥን በተመለከተ የተመረጠው ካምፓኒ የተሽከርካሪዎቹ ብቸኛ አስመጪ እና ጠጋኝ በመሆኑ አማራጭ ስላጡ የተከናወነ ግዥ መሆኑን እና በፕሮፎርማ ሆነ በሌሎች መንገድ የሚገዟቸው ግዥዎች የኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን የግዥ መመሪያን መሰረት ያደረገ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

- ለምርት አገልግሎት የሚውሉ የግብዓት ግዥዎችን በተመለከተ፡

➢ የውጪ ምንዛሬ እጥረት እና የኮንቴይነር ችግር በመኖሩ የግብዓት ግዥ በዕቅድ እንዳይመራ ስላደረገው በታሰበው ልክ እየተከናወኑ አለመሆኑን፣ በሪፖርቱ ከተዘ ረዘሩት ኬሚካሎች ውስጥ Aminotri-Methlene, activated alumina, palladium catalyst, tetrabutyl urea /TBU/, ethyl anthraquinone & aromatic solvent የመጠቀሚያ ጊዜ ማብቂያ የሌላቸውና ለረዥም ጊዜ ሳይበላሹ የሚቆዩ መሆናቸው፣ነገር ግን ሁለቱ ኬሚካሎች ማለትም trioctyl phosphate እንዲሁም በከፊል ethyl anthraquinone ለአንድ አመት ጊዜ ብቻ የሚቆዩ ኬሚካሎች ቢሆኑም መጠቀሚያ ጊዜያቸው ማለፍ በዋናነት የምርት ሂደቱ በተለያዩ ምክንያቶች በተገባው ደረጃ ባለመከናወኑ ኬሚካሉ በጊዜው ጥቅም ላይ ሳይውሉ በመቆየቱ የተከሰተ መሆኑን ይሁንና ኬሚካሉ አያያዙ በጥሩ ሁኔታ ከሆነ እስከ ሁለት ዓመት ያህል አገልግሎት ላይ መዋል እንደሚችል፣ሆኖም የአገልግሎት ጊዜያቸው አጭር የሆኑ ኬሚካሎች የመገልገያ ጊዜው ከማብቃቱ ጥቂት ወራት ውስጥ መጋዘን መድረሱ እውነታነት ያለው መሆኑን ገልፀዋል፡፡

24.ኃላፊዎቹ ይህንን ይበሉ እንጂ፡

- የተተካው ኮምፕሬሰር ከሁለት ዓመታት በላይ ያልተተከለና ርክክብ ያልተደረገ ከመሆኑም በላይ የተያዘው 60,000 ዶላር አሁን ካለው ከገንዘብ ፋይዳ አንፃር ሲታይ ተመጣጣኝ ባለመሆኑ እንዲሁም በፕሮፎርማ የሚገዛቸው ግዥዎች የኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን የግዥ መመሪያ መሰረት ያላደረገ በመሆኑ፤
- ለምርት አገልግሎት የሚውሉ የግብዓት ግዥዎችን በተመለከተ፡እ.ኤ.አ 26/07/2016 ተገዝተው የገቡ ኬሚካሎች በጠቅላላ 17,050 ኪሎግራም በክምችት እያለ በተጨማሪ እ.ኤ.አ 28/03/2022 በጠቅላላ 12,925 ኪሎግራም ተገዝተው አገልግሎት ሳይሰጡ በመቀመጣቸው፣ ኬሚካሎቹ ተከማችተው ያሉበት ሁኔታ ደህንነቱን ባልጠበቀ ቆርቆሮ መጋዘን መሬት ላይ ተደፍተው ያሉ በመሆናቸው እንዲሁም ኬሚካሎቹ በአምራች ድርጅቱ ከተቀመጠው አንጻር የአገልግሎች ጊዜ ያለፈባቸው በመሆናቸው የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

25.ፋብሪካው የኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን የግዥ መመሪያ ቁጥር 07/2012 የፕሮፎርማ ግዥ ህጎችን አለመተግበሩ እንደ ምክንያት የሚወሰድ ሲሆን ይህም ፋብሪካው የግብዓት ግዥዎችን በተፈለገው ጊዜ፣መጠን እና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ እንዳይፈፅም ምክንያት ሆኗል፡፡

26.ፋብሪካው የሚፈጽማቸው የፕሮፎርማ ግዥዎች የመንግስት ግዥ ህግና መመሪያን ያልተከተሉ በመሆናቸው እንዲሁም ለምርት አገልግሎት የሚውሉ የግብዓት ግዥዎችን ሲፈፅም በዕቅድ ያልተመራና በተፈለገው ጊዜ፣መጠን፣ጥራት እና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ ያልተከናወነ በመሆኑ ፋብሪካው የምርት ሂደቱ እንዲስተገዋጎል ያደረገ ሲሆን የአገልግሎት ግዜያቸዉ ያለፈባቸዉ የምርት ግብዓት ኬሚካሎች በብዛት የሚገኙ በመሆኑ ፋብሪካው ለአላግባብ ወጪ እንዲዳረግ አድርጎታል፡፡

## ፋብሪካው ተመሳሳይ ገቢ ምርቶችን በራሱ ማምረቱን በተመለከተ፤

27.ፋብሪካው ከውጭ ሀገር የሚገቡትን ተመሳሳይ ምርቶች (ግብዓቶችን) በፋብሪካው ሊያመርት ይገባል፡፡

28.ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-

- ፋብሪካው ከውጭ ሀገር የሚገቡትን ተመሳሳይ ምርቶች (ግብዓቶችን) በፋብሪካው ለማምረት የሚያስችሉ እንቅስቃሴዎችን/ሙከራዎችን/ ያላደረገ መሆኑ፤

- በፋብሪካውም ሆነ በኮርፖሬሽን በኩል አማራጭ የፖሊሲ አቅጣጫ በመፈለግና በማስጠናት የተለያዩ የኢንቨስትመንት አማራጮችን በመጠቀም ኢንቨስተሮችን ለመሳብ ጥረት ያላደረገ መሆኑ፤

29. ስለጉዳዩ የፋብሪካው የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ፤በረቂቅ ሪፖርት እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት መልስ፡-

- ከውጭ ሀገር የሚገቡትን ተመሳሳይ ምርቶች (ግብዓቶችን) በፋብሪካው አቅም ብቻ ተተኪ ምርቶችን ለማምረት ስለማይቻል፤ከውጪ ሃገር ባለሀብቶች ጋር ለመስራት ጆይንት ቬንቸር የጠየቁ መሆኑን እና ከዩንቨርስቲዎች ጋር በትብብር እየሰሩ መሆኑን እንዲሁም አስፈለጊ የፖሊሲ ግብዓቶችን ለሚመለከተው አካል የሰጡ መሆኑ፤ ብዙ ጥናቶች ያስጠኑ ቢሆንም አዋጪ አለመሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

30. የስራ ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጅ፡-

- ከውጭ ሀገር የሚገቡትን ተመሳሳይ ምርቶች በፋብሪካው ለማምረት ከባለሀብቶች ጋር በጆይንት ቬንቸር ለመስራት የተደረገውን ጥረት የሚያሳይና ለሚመለከተው አካል የተሰጠውን የፖሊሲ ግብዓቶች ማስረጃ ባለመቅርቡ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

31. ፋብሪካው በሚመለከታቸው አካላት የግብዓት ምርቶችን በአገር ውስጥ ለማምረት የአዋጭነት ጥናት በማስጠናት ጥናቶቹን ተግባራዊ ለማድረግ ባለመቻሉ እንዲሁም በሚመለከታቸው አካላት የፖሊሲ ድጋፍ እንዲያገኝ ጥረቶች ባለማድረጉ በኦዲቱ እንደ ክፍተት ለተወሰደው ፋብሪካው ተመሳሳይ ምርቶችን በራሱ ለማምረት እንዳይችል ለማድረጉ እንደ ምክንያትነት ሊወሰድ ይችላል፡፡

32. ፋብሪካው ከውጭ ሀገር የሚገቡትን ተመሳሳይ ምርቶች (ግብዓቶችን) በፋብሪካው የማያመርት በመሆኑ ለግብዓት እጥረትና ለከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ዳርጎታል፡፡

## የፋብሪካው ንብረት አያያዝ እና ተረፈ ምርት አወጋገድ በተመለከተ፤

33. ፋብሪካው የመንግስት ንብረት አያያዝ መመሪያን በመከተል የንብረት አስተዳደር ስርዓት እንዲሁም አገልግሎት ሊሰጡ የማይችሉ ንብረቶችንና ተረፈምርቶችን አወጋገድ ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

34. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-

- የፋብሪካው የንብረት አስተዳደር ስርዓት የተዘረጋ ቢሆንም በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በተደገፈ የንብረት ገቢና ወጪ ሂሳብ ምዝገባ የማያደርግ መሆኑ፤

➢ የፋብሪካው የመለዋወጫ መጋዘን የዕቃዎች እንቅስቃሴ መከታተያ /Stock Control Card/ ካርድ ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ የተቋረጠ መሆኑ፤

➢ ፋብሪካው አገልግሎት ሊሰጡ የማይችሉ ንብረቶችንና ተረፈምርቶችን አወጋገድ ስርዓት ተግባራዊ ያላደርገ መሆኑ፤ ለአብነት፡-

☞ ከተለያዩ የፋብሪካው ክፍሎች የተሰባሰቡ ቁርጥራጭ ብረታ ብረቶች፣ የአርማታ ብረቶች፣ የኤሌክትሪክ ኬብሎች፣የጋዝ ሲሊንደሮች ግራይንዲንግ ማሽኖች፣ድሪሊንግ ማሽኖችን ያላስወገደ መሆኑ፤

☞ እንዲሁም የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸውን ኬሚካሎች፤ የሰልፈርና የካኦሊን ኬክ ተረፈ ምርቶችን በአግባቡ የማያስወግድ መሆኑ፤





**ስዕል**1፡ በአግባቡ ያልተወገዱ የኬሚካል **ስዕል** 2፡ በአግባቡ ያልተወገዱ የካኦሊን ኬክ ተረፈ ምርት ማቀጣጠያ ካታሊስት ተረፈ ምርት

35.ስለጉዳዩ የፋብሪካው የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ፤በረቂቅ ሪፖርት እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት መልስ፡-

➢ ፋብሪካው ዘመናዊ የንብረት ስርዓትን በቴክኖሎጂ ለመደገፍ በውስጥ አቅም እየሰራ የሚገኝ መሆኑን፤ በኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮፖሬሽን ደረጃ ተገቢውን ቴክኖሎጂ ፓኬጅ (ERP) ለመጠቀም በሂደት ላይ እንደሚገኙ እንዲሁም የመለዋወጫ መጋዘን የእቃዎች እንቅስቃሴ መከታተያ ካርድ ታትሞ የመጣ ቢሆንም ካርዶቹ ስራ ላይ አለመዋላቸው ስህተት በመሆኑ በቀጣይ ታርሞ ስራ ላይ እንዲውሉ የሚደረግ መሆኑን፤

➢ የካኦሊን ኬክ ተረፈ ምርት በሽያጭ ለማሰወገድ የተጀመሩ እንቅስቃሰዎች የነበሩ ቢሆንም ያልተሳካ መሆኑን፤ በቀጣይ የተረፈ ምርቶቹ ያላቸውን ኢኮኖሚያዊና አካባቢያዊ ጠቀሜታ በጥናት በማስደገፍ ስራ ላይ የሚውሉበትን መንገድ ለማመቻቸት ጥረት እንደሚያደርጉ ገልፀዋል፡፡

36.ዘመናዊ የንብረት ስርዓትን በቴክኖሎጂ ለመደገፍ የሚያስችል የተደራጀ የውስጥ አቅም አለመኖር የንብረት አስተዳደር ስርዓቱን በቴክኖሎጂ እንዳይደገፍ በምክንያትነት የሚታይ ሲሆን የተረፈ ምርቶች በአግባቡ አለመያዝ እና አለመወገድ ከአካባቢም ሆነ ከጤና ጉዳት አንፃር ያላቸውን ተፅዕኖ በአግባቡ ለመከላከል ትኩረት አለመስጠት በኦዲቱ እንደ ክፍተት ለተወሰደው ተረፈ ምርቶቹን የሚያስወግድበት አሰራር ስርዓት በማዘጋጀት ተግባራዊ እንዲሆን ላለመደረጉ እንደ ምክንያትነት ሊወሰድ ይችላል፡፡

37.ፋብሪካው በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በተደገፈ የንብረት ገቢና ወጪ ሂሳብ ምዝገባ የማያደርግ በመሆኑ የንብረት አስተዳደር ስርዓት እንዳይተገበርና የንብረት እንቅስቃሴን በአግባቡ እንዳይከታተል ያደረገ ሲሆን አገልግሎት ሊሰጡ የማይችሉ ንብረቶችንና ተረፈምርቶችን የሚያስወግድበት ስርዓት ባለመዘርጋቱ ተረፈ ምርቶቹ ኢኮኖሚያዊና አካባቢያዊ ጠቀሜታ ሊያገኝ የሚገባውን ጥቅም ከማጣቱም በተጨማሪ በፋብሪካው ግቢ ውስጥ በየቦታው ተደፍተው የሚገኙ የካኦሊን ኬክ ተረፈ ምርት የግቢውን ገፅታ እያበላሸና በጸሐይ ጊዜ ስለሚያንጸበርቅ በሰው ዓይን ላይ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል፡፡

## የፋብሪካው የግንባታ ኮንትራት አስተዳደር ውሎች ስለመፈፀማቸው እና ክትትል ስለመደረጉ፤

38.የፋብሪካው ነባር ፋብሪካዎችን መልሶ የማቋቋም እና የሃይድሮጅን ፐርኦክሳይድ ፋብሪካ የግንባታ ፕሮጀክቶች ኮንትራት ውሉ ላይ በተቀመጠው መስፈርት /Specification/ እና በውል ሰነዱ የጥራት ስታንዳርድ መሰረት በተያዘላቸው በጀት እና ጊዜ ተገንብተው ወደ ምርት ማምረት ሂደት ሊገቡ ይገባል፡፡ እንዲሁም ይህንን በተመለከተ ፋብሪካው የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋና አስፈላጊውን የእርምት እርምጃ በወቅቱ ሊወስድ ይገባል፡፡

39.ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-

- <u>የፋብሪካው ፕሮጀክቶች ግንባታ በጀት እና በጊዜ ስለመፈፀሙ በተመለከተ፤</u>


- የአሉሚኒየም ሰልፌት እና የሰልፈሪክ አሲድ ፋብሪካዎችን መልሶ የማቋቋም ወይም የማደስ ሥራ በተያዘላቸው ጊዜ ያልተጀመረ መሆኑ፤ የሃይድሮጅን ፐርኦክሳይድ ፋብሪካ የግንባታ ፕሮጀክቶች በተያዘለት በጀት እና ጊዜ ያላለቀ መሆኑ፤ለማሳያ፡-

- **ከበጀት አንፃር**

  - የሃይድሮጂን ፐርኦክሳይድ ፋብሪካ ግንባታ በኮንትራት ውል ቁጥር 8720 ቀን 02/01/2012፤ የውል ስምምነት መሰረት ከውጭ ሀገር ለሚመጣ የማምረቻ መሣሪያ 7,323,100 የአሜሪካን ዶላር በወቅቱ በኢትዮጵያ የባንክ ምንዛሬ ተመን

DRAFT

17.4725 ብር 127,952,864.75 እና ለሀገር ውስጥ ወጪዎች ብር 14,152,725.00 በአጠቃላይ 142,105,589.75 ብር ይጠናቀቃል ተብሎ ውል የተገባ ቢሆንም ፋብሪካውን ገንብቶ ለማጠናቀቅ በአጠቃላይ የወጣው ወጪ 228,348,880.81 (ሁለት መቶ ሃያ ስምንት ሚሊዮን ሶስት መቶ አርባ ስምንት ሺህ ስምንት መቶ ሰማኒያ ብር ከሰማኒያ አንድ ሳንቲም) ነው፡፡ ይህም ከተገባው የ86,243,291.06 (የሰማኒያ ስድስት ሚሊዮን ሁለት መቶ አርባ ሦስት ሺህ ሁለት መቶ ዘጠና አንድ ብር ከስድስት ሳንቲም) ወይም 60.68% ጭማሪ ያለው መሆኑ፤




- **ከጊዜ አንፃር**
  - የሃይድሮጅን ፐርኦክሳይድ ግንባታ ፕሮጀክት በተገባው የኮንትራት ውል ቁጥር 8720 እ.ኤ.አ 02/01/2012 መሰረት በአንድ ዓመት(12 ወራት) መጠናቀቅ ሲገባው የፕሮጀክቱ የተጠናቀቀው እ.ኤ.አ 08/06/2016 ሲሆን ከውል አንፃር ስታይ አራት ዓመት ከአምስት ወር የዘገየ መሆኑ፤

☞ የሰልፈሪክ አሲድ እና የአሉምኒየም ሳልፌት መልሶ ማቋቋም ፕሮጀክት በተገባው የኮንትራት ውል ቁጥር 9570 ቀን 13/12/2021 መሰረት ስራው መጀመር ሲገባው ሳይጀመር ከአንድ ዓመት በላይ ያስቆጠረ መሆኑ፤

- ፋብሪካ የግንባታ ፕሮጀክቶች ኮንትራት ውሉ ላይ በተቀመጠው መስፈርት /Specification/ እና በውል ሰነዱ የጥራት ስታንዳርድ መሰረት ተገንብተው ወደ ምርት ማምረት ሂደት የገቡ ስለመሆናቸው ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡

- የሃይድሮጅን ፐርኦክሳይድ ፋብሪካ የግንባታ ፕሮጀክቶች ኮንትራት ውሉ ላይ በተቀመጠው መስፈርት /Specification/ እና በውል ሰነዱ የጥራት ስታንዳርድ መሰረት ተገንብተው ወደ ምርት ማምረት ሂደት ያልገባ መሆኑ፤ለአብነት፡-

☞ በሃድሮጅን ፐርኦክሳይድ ፋብሪካ ማምረቻ ዩኒት ከተተከሉ ሦስት የፕሮሰስ ኮምፕረሰሮች ውስጥ በተከላ ወቅት እክል በገጠመው አንዱ የፕሮሰስ ኮምፕሬሰር ምትክ የመጣው የፕሮሰስ ኮምፕሬሰር ያልተተከለ መሆኑ፤

☞ የፋብሪካውን የምርት ሂደት ለማረጋገጥ የወርኪንግ ሶሉሽን (working solution) ይዘት ለመለካት የሚያገለግለው "GC" የላብራቶሪ መሳሪያ የቴክኒክ ችግር ያለበት በመሆኑ የምርት ሂደትን በተገቢው ሁኔታ ማገዝ ያልተቻለ መሆኑ፤

- ከላይ የተገለፁት ችግሮች በፋብሪካው ፕሮጀክቶች ላይ የተከሰቱ ቢሆንም የፋብሪካው የግንባታ ፕሮጀክቶቹ በገቡት ውል መሰረት መፈጸማቸውን ያልተከታተለና አስፈላጊውን የእርምት እርምጃ በወቅቱ ያልወሰደ መሆኑ በኦዲት ወቅት ታይቷል፤

40.ስለጉዳዩ የፋብሪካው የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ፤በረቂቅ ሪፖርት እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት መልስ፡-

- የበጀት እና የውጭ ምንዛሬ በጊዜ ካለመፈቀዱ ጋር ተያይዘው ኤልሲ(LC)ለመክፈት በፋብሪካው በኩል አንድ ዓመት ተኩል ገደማ የዘገየ መሆኑ፤በኮንትራክተሩ በኩል የሲቪል ግንባታ መዘግየት፤የኤሌክትሪክ አቅርቦት ለማግኘት ረዥም ጊዜ እስከ እ.ኤ.አ የካቲት 2016 የዘገየ በመሆኑ ፕሮጀክቶቹን ከታቀደላቸው በጀትና ጊዜ አንፃር ለማስፈፀም አለመቻሉን፤
- እንዲሁም ለኮንትራክተሩ በተገባዉ ውል መሠረት ከተከፈለው ገንዘብ በተጨማሪ ለፕሮጀክት ቢሮ ግንባታ፣ ለተሸከርካሪዎች ግዥ እና ለጥሬ ውሃ ዝርጋታ የተከፈለ መሆኑ፤
- ኮምፕሬሰሮችን በተመለከተ የቀረበው አስተያየት እውነትና ተቀባይነት ያለው መሆኑን፤

➢ GC" የላብራቶሪ መሳሪያ የቴክኒክ ችግር በስራ ሂደት ወቅት በተከሰተ ስህተት የተበላሸ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

41. ኃላፊዎቹ ይህንን ይበሉ እንጂ ከባንክ ጋር ተያይዘው ተከፍለዋል የተባሉ ክፍያዎች ፕሮጀክቱ በመዘግየቱ የመጡ ተጨማሪ ወጪዎች በመሆናቸው እንዲሁም ከዛ ውጪ የተጠቀሱ ክፍያዎች (ለምሳሌ ለፕሮጀክት ቢሮ ግንባታ፣ ለተሸከርካሪዎች ግዥ፣ ለጥሬ ውሃ ዝርጋታ፣ ለአማካሪ ...) ክፍያ ከተፈፀመላቸው አካላት ጋር የተደረገ የውል ስምምነት ማስረጃዎች ያልቀረቡ እንዲሁም ለፕሮጀክቱ ከተያዘው በጀት አንፃር ጭማሪ የተፈፀሙ ወጪዎች በመሆናቸው፤ ለኮምሽኒንግ ተከፈለ የተባለው ተጨማሪ ክፍያ በኮንትራት ውል ተካቶ የነበረ ስራ እና በኮንትራክተሩ ሊሸፈን የሚገባ በመሆኑ ምላሻቸውን አልተቀበልነውም፡፡

42. ፋብሪካው ለፕሮጀክቶቹ አፈፃፀም ያለበትን የመከታተል ሃላፊነት ትኩረት ሰጥቶ ባለመፈፀሙ ተገቢውን ክትትል በማድረግ በወቅቱ የእርምት እርምጃ ላለመውሰዱ እንደ ምክንያትነት የሚጠቀስ ሲሆን ይህም በኦዲቱ እንደ ክፍተት ለተወሰደው ፕሮጀክቶቹ በተባለላቸው ጊዜ እና በጀት እንዳይፈፀሙ ምክንያት ሆኗል፡፡

43. ፋብሪካው የግንባታ ፕሮጀክቶቹ በገቡት ውል መሰረት ያልተፈፀሙ እና አስፈላጊው የእርምት እርምጃ በወቅቱ ባለመወሰዱ ፋብሪካውን ለተጨማሪ ወጪና ጊዜ መዘግየት ያስከተለ ሲሆን በምርመራ ሂደት (ፕሮሲጀር) መሠረት በሳምንት ሁለት ጊዜ ያህል መከናወን የሚገባው ምርመራ በላብራቶሪ መሳሪያ ("GC") ባለመስራቱ በወርና ከዛ በላይ በሆነ ጊዜ እየተሰራ በመሆኑ በምርት ኦፕሬሽን ሂደት ላይ አላስፈላጊ ጫና እና መስተጓጉል እንዲፈጠር አድርጓል፡፡

## ግንባታው የተጠናቀቀ ፕሮጀክት ርክክብን በተመለከተ፤

44. ፋብሪካው ግንባታቸው የተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች የመጨረሻ ርክክብ በውሉ መሰረት ተግባራዊ በማድረግ የታዩ ግድፈቶች /Defects/ ካሉ ህጋዊ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

45. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-

➢ ፋብሪካው ግንባታው የተጠናቀቀውን የሃይድሮጅን ፐርኦክሳይድ ፕሮጀክትን አስፈለጊውን ፎርማሊት መሟላቱን በማረጋገጥ የመጨረሻ ርክክብ ሳይደረግ ከአስር ዓመታት በላይ የቆየና በታዩ ግድፈቶች ላይ /Defects/አስፈላጊውን/ ህጋዊ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፤ለአብነትም፡-

☞ የሃይድሮጅን ፐርኦክሳይድ ፋብሪካ የግንባታ ሂደትን በተመለከተ በቴክኒካል ኮሚሽኒንግ ኮሚቴ (TECHNICAL AND COMMISSIONING TEAM)፤ በግንባታ ማጠናቀቂያ (ERECTION COMPLETION)፣የፋብሪካ ሙከራ (PRFORMANCE GUARANTEE TESTS)፣የአፈፃፀም ሙከራ (PROVISIONAL ACCEPTANCE)፣ በጊዜዊ ርክክብ ወቅት በእ.ኤ.አ 08/06/2016 የተለዩ ዋና ችግሮች በወቅቱ መስተካከላቸውን ኮሚቴው በድጋሚ ያረጋገጠበት ሪፖርት ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤

46.ስለጉዳዩ የፋብሪካው የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ፤በረቂቅ ሪፖርት እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት መልስ፡-

- የተጠቀሱት ክፍተቶች በርክክብ ወቅት የታዩና በቀጣይ በተለያዩ ጊዜ እንዲስተካከሉ የተደረጉ መሆናቸውን ይሁንና ኮንትራክተሩ በተበላሸው ምትክ የተካው ኮምፕሬሰር ተክሎና ፈትሾ ባለማስረከቡ የፕሮጀክቱ የመጨረሻ ርክክብ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ህጋዊ ዕርምጃ ከመውሰድ አንጻር አብዛኛው ችግር የአሰሪው ድርጅት ቢሆንም ድርጅቱ የፋብሪካው ቴክኖሎጂ አቅራቢ በመሆኑና ኦፕሬሽን ችግር ሲፈጠር፣ መለዋወጫ አቅርቦት እና ኬሚካል አቅርቦት ላይ ሌላ አማራጭ አስተማማኝ አቅራቢ እስካሁን ባለመገኘቱ ችግሩን በመግባባት መፈጸም ወይም መፍታት እንደ አንድ አማራጭ መንገድ ተደርጎ በማኔጅመንት መወሰዱን ገልፀዋል፡፡

47.ኃላፊዎቹ ይህንን ይበሉ እንጂ፡-

- ከኮንትራክተሩ ጋር ያለውን መልካም ግንኙነት ላለማበላሸት ተብሎ ግንባታው የተጠናቀቀ ፕሮጀክት የመጨረሻ ርክክብ በውሉ መሰረት ኦዲቱ እስከ ተጠናቀቀበት ተግባራዊ ሳይደረግ ከአስር አመታት በላይ በመቆየቱና በታዩ ግድፈቶች /Defects/ ላይም ህጋዊ እርምጃ አለመውሰዱን የኦዲት ቡድኑ አግባብ ሆኖ ባለማግኘቱ እንዲሁም የሃይድሮጅን ፐርኦክሳይድ ፋብሪካ የግንባታ ሂደትን በተመለከተ በቴክኒካል ኮሚሽኒንግ ኮሚቴ (TECHNICAL AND COMMISSIONING TEAM)፤ በግንባታ ማጣናቀቂያ (ERECTION CMPLETION)፣ የፋብሪካ ሙከራ (PRFORMANCE GUARANTEE TESTS)፣ የአፈፃፀም ሙከራ (PROVISIONAL ACCEPTANCE)፣ በጊዜዊ ርክክብ ወቅት በእ.ኤ.አ 08/06/2016 የተለዩ ዋና ችግሮች መስተካከላቸውን ኮሚቴው በወቅቱ በድጋሚ ያረጋገጠበት ሪፖርት ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

DRAFT

48. ፋብሪካው ወቅታዊ ምላሽ የሚያስፈልጋቸውን ጉዳዮች ለመወሰን እና የታዩ ግድፈቶች ላይ ህጋዊ እርምጃ ለመውሰድ ቁርጠኝነት አለመኖር በኦዲቱ እንደ ክፍተት ለተወሰደው ግንባታው የተጠናቀቀው የሃይድሮጅን ፐርኦክሳይድ ፕሮጀክት በውሉ መሰረት የመጨረሻ ርክክብ በማድረግ በታዩ ግድፈቶች ላይ ህጋዊ እርምጃ ላለመወሰዱ እንደምክንያትነት ሊጠቀስ ይችላል፡፡

49. ፋብሪካው ግንባታቸው የተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች የመጨረሻ ርክክብ በውሉ መሰረት ተግባራዊ በማድረግ በታዩ ግድፈቶች /Defects/ ላይ ህጋዊ እርምጃ ባለመውሰዱ ፕሮጀክቱ በውል መሠረት በጊዜ እና በተቀመጠላቸው ጥራት እንዳይጠናቀቅ ከማድረጉም በተጨማሪ የምርት ሂደቱ በታቀደው ልክ እንዳይሄድና እንዲስተጓጎል አድርጎታል፡፡

**የፋብሪካው የጥገና ስርዓትን በተመለከተ፤**

50. ፋብሪካው ውጤታማ የሆነ የጥገና(maintenance) ስርዓት በመዘረጋት አስፈላጊ የመለዋወጫ (የጥገና መሳሪያዎችን) በመያዝ የምርት ሂደቱ እንዳይስተጓጎል ሊያደርግ ይገባል፡፡

51. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-

- ፋብሪካው የመለዋወጫ እቃ እጥረት ያለበት በመሆኑ የምርት ሂደቱ የተስተጓጎለ መሆኑ፤ለማሳያ ከ2010 ዓ.ም እስከ 2014 ዓ.ም ድረስ በአጠቃላይ 82,194.94 የባከነ/ሥራ ላይ ያልዋለ/ ሰዓት (Down time) የተመዘገበ መሆኑ፤
- በፋብሪካው ተከላ ወቅት መጥተው በትርፍነት የተቀመጡ እና በተለያዩ ደረጃ ለፋብሪካው እድሳት(MAINTENANCE) የሚያገለግሉ መጠናቸው በርከት ያለ አሲዳማነትን የሚቋቋሙ ጡቦች፤/ACID RESISTANT BRICKS፤አሲድ መቋቋም የሚችል የሴራሚክ ሰድላ /ACID RESISTANT CERAMIC TILES/፤የኢንሱሌሽን ማት /INSULATION MAT/ እና ሌሎችም ዕቃዎች በሼድ/ በመጋዘን ውስጥ በአግባቡ ያልተቀመጡ መሆኑ፤

52. ስለጉዳዩ የፋብሪካው የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ፤በረቂቅ ሪፖርት እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት መልስ፡-

- በምንዛሬ ችግር ምክንያት መለዋወጫዎችን መግዛት ያልቻለ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

53. ፋብሪካው በመለዋወጫ እቃ እጥረት ምክንያት 82,194.94 የባከነ/ሥራ ላይ ያልዋለ/ ሰዓት (Down time) ለማስመዝገቡ እንደ ምክንያትነት ተወስዷል፡፡

54. ፋብሪካው በቂ የሆነ የመለዋወጫ ዕቃ (የጥገና መሳሪያዎችን) ባለመያዙ የምርት ሂደቱ እንዲስተጓጉል አድርጓል፡፡

DRAFT

***የገበያ መዳረሻ ጥናትን በተመለከተ፤***

55.ፋብሪካው ለሚያመርታቸው የኬሚካል ምርቶች በየወቅቱ ደሰሳ ጥናት በማድረግ የገበያ ድርሻውን በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ሊያሳድግ ይገባል፡፡

56.በኦዲቱ ወቅት፡-

- ፋብሪካው ለሚያመርታቸው የኬሚካል ምርቶች የሀገር ውስጥ ደሰሳ ጥናት በ2012 ዓ.ም እና በ2013 ዓ.ም ያደረገ መሆኑ፤

ነገር ግን፡

- በ2014 ዓ.ም ጥናት ያላደረገና ተጨማሪ የገበያ መዳረሻዎችን በሀገር ውስጥ ያላሰፋ መሆኑ፤ እንዲሁም ከ2012 እስከ 2014 ባሉ ዓመታት በውጭ ሀገር የደሰሳ ጥናት ያላደረገና ተጨማሪ የገበያ መዳረሻችን ያልፈጠረ መሆኑ፤በዚህም
  - ☞ በ2012 ዓ.ም በጀት ዓመት ለውጭ ሀገር ሽያጭ በመጠን 408 ቶን ማለትም 200 ቶን ሰልፈሪክ አሲድ እና 208 ቶን ሃይድሮጅን ፐርኦክሳይድ በብር 3,897,000 ለመሸጥ ታቅዶ 52.2 ቶን በመጠን እና በዋጋ 604,000 ብር በመሸጥ የዕቅዱን በመጠን 25.3%፤በዋጋ 21.5% ብቻ ያከናወነ መሆኑ፤
  - ☞ በ2013 በጀት ዓመት ከውጭ ንግድ 114,000 ሺ.ህ ዶላር የውጭ ምንዛሬ ለማስገኘት ታቅዶ ምንም ያልተገኘ መሆኑ፤
  - ☞ በ2014 በጀት ዓመት 240 ቶን ሰልፈሪክ አሲድ እና 208 ቶን ሃድሮጅን ፐርኦክሳይድ በአጠቃላይ 448 ቶን ምርት በብር 8 ሚሊዮን ለውጭ ሀገር ሽያጭ ለማከናወን ዕቅድ የተያዘ ቢሆንም ሽያጭ ያልተከናወነ መሆኑ፤ታውቋል፡፡

57.ስለጉዳዩ የፋብሪካው የበላይ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ መጠይቅ፤በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት መልስ፡-

- በ2014ዓ.ም በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር የገበያ ጥናት ያልተደረገና ተጨማሪ የገበያ መደረሻዎች ያልተፈጠረ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

58.የገበያ መዳረሻ ጥናት ለምርት ሽያጭ አፈፃፀም ያለውን አስተዋፅኦ በመረዳት ማስፈፀም አለመቻል በኦዲቱ እንደ ክፍተት ለተወሰደው ፋብሪካው ለሚያመርታቸው የኬሚካል ምርቶች የሽያጭ መዳረሻዎችን ለማስፋት እንዳይችል ላለመደረጉ እንደ ምክንያትነት ይጠቀሳል፡፡

59.ፋብሪካው ለሚያመርታቸው የኬሚካል ምርቶች በየወቅቱ የደሰሳ ጥናት ባለማድረጉ እና የገበያ መዳረሻዎችን (በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር) ባለማስፋቱ ከገበያ ድርሻው ሊያገኝ የሚገባውን ገቢ እንዲያጣ አድርጓል፡፡

DRAFT


**የፋብሪካው ምርቶች አቅርቦትን በተመለከተ፤**

60. ፋብሪካው ጥራት ያላቸውን የኬሚካል ምርቶችን ለማምረት የሚያስችል የጥራት ቁጥጥር በማድረግ እንዲሁም በማምረት አቅሙ (Attainable Design Capacity) ልክ በማምረት እና ምርታማነቱን በማሳደግ ከተለያዩ ድርጅቶ ጋር የተገባው የምርት አቅርቦት ውል መሰረት በወቅቱ ሽያጭ ሊፈፅም ይገባል፡፡

61. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-


- <u>ፋብሪካው ሊደርስበት ከሚችለው የማምረት አቅም (Attainable Design Capacity) ልክ ምርት ማምረቱን በተመለከተ፤</u>
  - ፋብሪካው አሉሚኒየም ሰልፌት፤ሰልፈሪክ አሲድ እና ሃይድሮጅን ፐርኦክሳይድ ኬሚካሎችን ዘመናዊ የአመራረት ቴክኖሎጂን በመጠቀም ሊደርስበት ከሚችለው የማምረት አቅም (Attainable Design Capacity) ልክ የማያመርትና የማይሸጥ መሆኑ፤ለማሳያነት፡-
    - ☞ ፋብሪካው ከ2012 ዓ.ም እስከ 2014 ዓ.ም በጀት ዓመታት ባለው ጊዜ አጠቃላይ 42,926 ቶን ምርትን ለማምርት፡-ማለትም አሉሙኒየም ሰልፌት በመጠን 18,913 ቶን ሰልፈሪክ አሲድ በመጠን 18,081 ቶን እና ሃይድሮጂን ፔርኦክሳይድ በመጠን 5,932 ቶን ኬሚካል ምርቶችን ለማምርት ያቀደ ቢሆንም ፋብሪካው ማምረት የቻለው አጠቃላይ በመጠን 14,429.1 ቶን ማለትም አሉሙኒየም ሰልፌት 5,894 ቶን ሰልፈሪክ አሲድ 6,967.96 ቶን እና ሃይድሮጂን ፔርኦክሳይድ 1,567.14ቶን በማምረት የዕቅዱን በመጠን 33.61% ያከናወነ መሆኑ፤ ከዕቅድ አንፃር 28,496.9 ቶን ማምረት የነበረበትን ምርት ያላመረተ መሆኑ፤ (ዝርዝሩ በአባሪ 4 ተያይዟል፡፡)


| ተ.ቁ | የተመረቱ የምርቶች አይነት | ከ2012 ዓ.ም እስከ 2014 ዓ.ም በጀት ዓመት ድረስ ያለው የምርት ዕቅድ፣ ክንውንና አፈጻጸም | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | በመጠን | | | |
| | | መለኪያ | ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም (%) |
| 1 | አሉሚኒየም ሳልፌት | በቶን | 18,913 | 5,894 | 31.16 |
| 2 | ሳልፈሪክ አሲድ | " | 18,081 | 6,967.96 | 38.54 |
| 3 | ሃይድሮጅን ፐርኦክሳይድ | " | 5,932 | 1,67.14 | 26.42 |
| | ድምር | " | 42,926 | 14,429.1 | 33.61 |




- ፋብሪካው ከሽያጭ ሊያገኘው የሚገባው ገቢ መገኘቱን በተመለከተ፤
  - ☞ ፋብሪካው ከ2012 እስከ 2014 በጀት ዓመታት ባለው ጊዜ አልሙኒየም ሰልፌት በመጠን 17113 ቶን፣ሰልፈሪክ አሲድ በመጠን 7165 ቶን እና ሃይድሮጂን ፐርኦክሳይድ በመጠን 6030 ቶን በድምሩ 30308 ቶን ኬሚካል ምርቶችን ለገበያ በማቅረብ 563,332,120 ገቢ በብር ማስገኘት ሲገባው ፋብሪካው ለገበያ ያቀረበው በመጠን 12,595.282 ቶን ማለትም አሉሙኒየም ሰልፌት 6,594.35 ቶን በብር 163,406,552.95፣ ሰልፈሪክ አሲድ 4842.372 ቶን በብር 82,701,569.45 እና ሃይድሮጂን ፐርኦክሳይድ 1158.56 ቶን በብር 39,227,988 በማቅረብ በገንዘብ 285,336,110.40፤ ገቢ በማስገባት የዕቅዱን በመጠን 41.55%፤በዋጋ 50.65% ያከናወነ መሆኑ፤ ከዕቅድ አንፃር <u>277,996,009.60</u> ማግኘት የነበረበትን ገቢ ያጣ መሆኑ፤

| ተ.ቁ | የተሸጡ የምርቶች አይነት | ከ2012 ዓ.ም እስከ 2014 ዓ.ም በጀት ዓመት ድረስ ያለው የሽያጭ ዕቅድ፣ ክንውንና አፈጻጸም | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በመጠን(በቶን | | | | በዋጋ(በብር) | | | |
| | | መለኪያ | ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም (%) | መሊኪያ | ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም (%) |
| 1 | አሉሚኒየም ሳልፌት | በቶን | 17,113 | 6,594.35 | 38.53 | በብር | 282,571,500 | 163,406,552.95 | 57.83 |
| 2 | ሳልፈሪክ አሲድ | " | 7,165 | 4,842.372 | 67.58 | " | 121,107,075 | 82,107,569.45 | 67.80 |
| 3 | ሃይድሮጅን ፐርኦክሳይድ | " | 6,030 | 1,158.56 | 19.21 | " | 159,653,545 | 39,227,988 | 24.57 |
| | ድምር | " | 30,308 | 12,595.282 | 41.56 | " | 563,332,120 | 285,336,110.40 | 50.65 |



## ➕ የፋብሪካው የምርት ጥራትን በተመለከተ፤

- ፋብሪካው ከ2012 ዓ .ም እስከ 2014 ዓ.ም ባለው ጊዜ የጥራት ቁጥጥር አስተዳደር ሥርዓት (ISO 9001:2015) የምስክር ወረቀት ያገኘ ቢሆንም ከአስተዳደር ስርዓት ከመዘርጋቱ በተጨማሪ የሚያመርታቸው  ምርቶች በዓለምአቀፍ ደረጃ ጥራቱን በጠበቀና ተወዳዳሪ በሆነ መልኩ እያመረቱ ስለመሆኑ በሚመለከታቸው አካላት ቁጥጥር እየተደረገ የማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ያላገኙ መሆኑ፤
- ፋብሪካው የኬሚካል ምርቶቹን ከሸጠ በኃላ የኬሚካል አያያዝና አጠቃቀም ጋር በተያያዘ የጥራት ጉድለት እንዳይከሰት ግንዛቤ የማይፈጥር እና የደንበኞችን ቅሬታ በአግባቡ የማያስተናግድ መሆኑ፤ ለአብነት፡-
  - ☞ ደንበኞች የሰልፈሪክ አሲድ ምርት ከገዙ በኃላ የመልክ ለውጥ (COLOUR Change) የሚታይ መሆኑ እና በሃይድሮጅን ፐርኦክሳይድ የምርት ጥራት (concentration) 50% በታች የሚሆንበት ሁኔታ ቢኖርም የጥራት ጉድለቱ ከፋብሪካው ወይም ከደንበኞች አያያዝ ጉድለት የተፈጠረ ስለመሆኑ የማጣራት ስራ ያልሰራ መሆኑ፤

## ➕ ፋብሪካው ከተለያዩ ድርጅቶች ጋር የገባውን የኬሚካል ምርቶች አቅርቦትን በተመለከተ፤

- ፋብሪካው ከተለያዩ ድርጅቶች ጋር የገባውን የኬሚካል ምርቶች አቅርቦት በገባው ውሉ መሰረት በወቅቱ መፈፀም ባለመቻሉ ውል ያቋረጠ መሆኑ፤ ለአብነት በተገባው ውል መሰረት የኬሚካል አቅርቦት ያልተፈፀመላቸው ድርጅቶች ውስጥ፡-
  - ☞ አዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ  ባለስልጣን ጋር በ2009 ዓ.ም ከገባው ውል ውስ 1414 ቶን አልሙኒየም ሰልፌት ያላቀረበ መሆኑ፤
  - ☞ አዳማ ከተማ መጠጥ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ድርጅት ጋር ከገባው ውል ውስጥ 85 ቶን አልሙኒየም ሰልፌት ያላቀረበ መሆኑ፤
  - ☞ ሻሸመኔ ከተማ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት መ/ቤት ጋር ከገባው ውል ውስጥ 180ቶን አልሙኒየም ሰልፌት ያላቀረበ መሆኑ፤
  - ☞ ሐዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክ ጋር ከገባው ውል ውስጥ 14 ቶን አልሙኒየም ሰልፌት እና 314.41 ቶን ሰልፈሪክ አሲድ ያላቀረበ መሆኑ፤ እንዲሁም

DRAFT

☞ ለጅማ ከተማ ውሃ አገልግሎት እና ለበደሌ ከተማ ውሃ አገልግሎት በፊት ያቀርብ የነበረውን አልሙኒየም ሰልፌት ምርት ከ2014 ዓ.ም ጀምሮ ያቋረጠ መሆኑ፤

ከተከለሱ የሰነድ ማስረጃዎች ታውቋል፡፡

62.ስለጉዳዩ የፋብሪካው የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ፤በረቂቅ ሪፖርት እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት መልስ፡-

- የነባሮቹ ፋብሪካዎች በእርጅና ምክንያት ዋና ዋና ማሽኖች የቴክኒካል ችግር ያለባቸው በመሆኑ፤ የጥሬ ዕቃ አቅርቦት ችግር፤ የሃይድሮጅን ፐርኦክሳይድ ምርት በሀገር ውስጥ እና በውጭ ሀገር የገበያ ልምድ ውስንነት ያለበት መሆኑና በውጭ ገበያ ላይ ለመሳተፍ የማሸጊያ ጀርካን ጥራት ጉድለት ያለው መሆኑን፤
- ምርቶቹ በስታንዳርዱ መሰረት እያመረቱ ስለሆነ የጥራት ችግር የማይፈጠር መሆኑን ይሁን እንጂ ምርቶቹ በሚቆዩበት ጊዜ የኬሚካሎቹ ጥንካሬ (ኮንስንትሬሽን) መቀነስና ከአያያዝ ጉድለት የመልክ ለውጥ ሊከሰት እንደሚችል፤
- በአሁኑ ወቅት ምርት እየተመረተ ስለሆነ ውል ለተቋረጠባቸው ድርጅቶች ምርት ማቅረብ መጀመራቸውን ገልፀዋል፡፡

63.የስራ ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ፡-

- ውል ለተቋረጠባቸው ድርጅቶች ምርት ማቅረብ የጀመረ ቢሆንም የምርት ሂደቱ በጥሬ ዕቃ አቅርቦትና በቴክኒክ ችግሮች ምክንያት የምርት ሂደቱ አሁንም እየተስተጓጎለና ችግሩ በዘላቂነት ያልተወገደ በመሆኑ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

64.ፋብሪካው ለሚያመርተው ምርቶች የጥራት ማረጋገጫ አካሄዶችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ያልተገበሩ በመሆኑ በደንበኞቻቸው ለቀረቡ ችግሮች እንደምክንያትነት ሊጠቀስ የሚችል ሲሆን የፋብሪካው መሳሪያዎች ቴክኒካል ችግሮች በወቅቱ እንዲፈቱ አስቸኳይ አፈፃፀሞች እንዲከናወኑ ባለመደረጉ እና የፋብሪካውን አመራረት የማዘመን ስራዎች ባለመሰራታቸው በኦዲቱ ወቅት እንደ ክፍተት ለተወሰደው ፋብሪካው በማምረት አቅሙ ልክ በማምረት የሚፈለግበትን አቅርቦት በውሉ መሰረት ለማቅረብ እንዳይችል ስለማድረጉ እንደ ምክንያት ሊወሰድ ይችላል፡፡

65.ፋብሪካው በሰልፈሪክ አሲድ እና በሃይድሮጂን ፐርኦክሳይድ ምርቶች ላይ ከአያያዝ ጉድለት የኮንስንትሬሽን መቀነስና የጥራት ችግር እንዲፈጠር እንዲሁም ምርታማነቱን ባለማሳደጉና ሊደርስበት ከሚችለው የማምረት አቅም (Attainable Design Capacity) ልክ በሦስት ዓመታት ውስጥ 30,308 ቶን ባለማምረቱና ባለመሸጡ ብር 277,996,009.60 ማግኘት

የነበረበትን ገቢ እንዲያጣ እና ከተለያዩ ድርጅቶች ጋር የገባውን የኬሚካል ምርቶች አቅርቦት በገባው የውል ኮንትራት መሰረት በወቅቱ መፈፀም እንዳይችል እንዲሁም በፋብሪካው ሊመረቱ የሚችሉ አልሙኒየም ሰልፌት እና ሰልፈሪክ አሲድ ምርቶች ከውጪ በውጭ ምንዛሪ ወጪ እንዲገዙ አድርጎታል፡፡

**የምርት ማሸጊያ ጀርካን ጥራትን በተመለከተ፤**

66. ፋብሪካው የተጠናውን የጀሪካን ፋብሪካ በመገንባት ጥራታቸውና ደህንነታቸው የተጠበቀ የኬሚካል ምርት ማሸጊያ ጀሪካኖች ሊያመርት ይገባል፡፡

67. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-

- የጀሪካን ማምረቻ ፋብሪካ ለመገንባት በ2012፣በ2013 እና በ2014 በጀት ዓመታት አቅዶ እስካሁን ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፣
- በጨረታ ከሀገር ውስጥ አቅራቢ የሚገዛው ጀሪካን የጥራት ችግር፣የዋጋ ውድነትና የአቅርቦት ችግር ያለበት መሆኑ፤ለማሳያ፡-
  - ☞ ፋብሪካው የሚጠቀመው የኬሚካል ማሸጊያ ጀሪካን የጥራት ችግር (የማፍሰስና የመሰንጠቅ) እንዲሁም አቅርቦት እጥረት ምክንያት በፋብሪካው ውጤታማነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያስከተለ መሆኑ፣

68. ስለጉዳዩ የፋብሪካው የበላይ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ መጠይቅ እና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ወቅት በሰጡት መልስ፡-

- የጀሪካን ጥራትና የአቅርቦት ችግር ለመቅረፍ የጀሪካን ፋብሪካ ለመገንባት አቅደው እየተንቀሳቀሱ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

69. የጀሪካን ማምረቻ ፋብሪካ የሚሆን በጀት በመመደብ ፋብሪካው እንዲቋቋም አለመደረጉ በኦዲቱ እንደ ክፍተት ለተወሰደው ጥራት ያላቸው የጀሪካን ምርቶች ለማምረት እንዳይቻል ለማድረጉ እንደምክንያትነት ሊጠቀስ ይችላል፡፡

70. ፋብሪካው የጀሪካን ማምረቻ ግንባታ ተግባራዊ ባለማድረጉ ጥራታቸውና ደኅንነታቸው የተጠበቀ የኬሚካል ምርት ማሸጊያ ጀሪካኖች እንዳይጠቀም እና በድርጅቱ ውጤታማነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዲፈጠር አድርጓል፡፡

**የፋብሪካው የአካባቢ፣የጤና እና ደህንነት አያያዝ ስርዓት ተግባራዊ ስለመሆኑ፤**

71. ፋብሪካው የአካባቢ አስተዳደር በመዘርጋት የደረቅ ቆሻሻ፣የፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ፣የአየር ብክለት መከላከል ስራዎችን ሊሰራ እንዲሁም የጤና እና ደህንነት ስርዓትን በመዘርጋት ለሠራተኞቹ የአደጋ መከላከያ ትጥቆች፣አልባሳትን በወቅቱና በተፈለገ ጊዜ በማቅረብ በሥራ ላይ የሚደርሱ ጉዳቶችን በመከላከል ደህንነቱ የተጠበቀ የሥራ አካባቢን ሊፈጥር ይገባል፡፡

72. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-

- <u>የፋብሪካው የአካባቢ አስተዳደር ደህንነት ስርዓትን በተመለከተ፤</u>
  - ፋብሪካው ውጤታማ የሆነ የአካባቢ አስተዳደር ደህንነት ስርዓት (Environmental Management System) ISO 14001፡2015 ሂደት ተግባራዊ ያላደረገና የምስክር ወረቀት (ሠርትፊኬት) ያላገኘ መሆኑ፤
  - ፋብሪካው የአካባቢ ደኅንነት ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት (Environmental Impact Assessment) ያላካሄደ መሆኑ፤
  - ፋብሪካው የደረቅ ቆሻሻ፤ አያያዝና አወጋገድ ስራዎችን ያልሰራ መሆኑ፤ለአብነትም፡-
    - ☞ ለደረቅ ቆሻሻ እና ለሰልፈር ተረፈ ምርት መለያና ማስወገጃ እንዲያገለግል ግንባታው የተጀመረው የኮንስትራክሽን ሥራ ኦዲቱ እስከ ተጠናቀቀበት ያላለቀ በመሆኑ በፋብሪካው ግቢ ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች ላይ እጅግ ከፍተኛ የሆነ የካኦሊን ፊልተር ኬክ እና የሰልፈር /ድኝ/ ተረፈ ምርቶች ተደፍተው የሚታዩ መሆኑ፤



DRAFT

ስዕል 3፡ በአግባቡ ያልተወገደ የሰልፈር ስዕል 4፡ተረፈ ምርት መለያና ማስወገጃ ታስቦ ያላላቀግንባታ /ድኝ/ ተረፈ ምርት

☞ በፋብሪካው የደረቅ ቆሻሻ አያየዝና አወጋጋድ ላይ በቂ ቁጥጥርና ክትትል እየተደረገ አለመሆኑ፤

➢ ፋብሪካው የፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስራዎችን ያልሰራ መሆኑ፤

☞ ፋብሪካው ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የፍሳሽ ቆሻሻ ማከሚያ (treatment plant) የሌለው በመሆኑ የፋብሪካው ፍሳሽ ውጋጅ የተቀመጠውን ደረጃ ባሟላ መልኩ ተጣርቶ መውጣቱን ለመቆጣጠርና ለመከታተል ያልቻለ መሆኑ፤

➢ ፋብሪካው የአየር ብክለት መከላከል ስራዎችን ያልሰራ መሆኑ፤ለምሳሌ

☞ ፋብሪካው የጋዝ ልቀት መጠንን የሚያሣይ ጋዝ አናላይዘር መሣሪያ የሌለው በመሆኑ በአይን የሚታዩና የማይታዩ በካይ የሆኑ ጋዞች አምልጠ በሚወጡበት ወቅት ለመቆጣጠር የሚያስቸግር መሆኑ፤

- <u>የጤናና ደህንነት ስርዓት ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፤</u>

➢ ፋብሪካው የሙያ ደኅንንትና ጤንነት ሥርዓት ISO 45001፡2018 (Occupational Safety and Health Management) በስታንዳርዱ መሰረት ያልተገበረና የምስክር ወረቀት ያላገኘ መሆኑ፤

➢ ፋብሪካው የሙያና የኢንዱስትሪውን ደህንነት በመከታተልና በማስጠበቅ የአደጋ መከላከያ መሣሪያዎችን በማዘጋጀት፤የአደጋ መከላከያ መሣሪያዎችን ብቃት በማረጋገጥ፣ የሥራ አልባሳትንና የደህንነት ዕቃዎችን በወቅቱ በማሟላት በሥራ ላይ የሚደርሱ ጉዳቶችን ያልተከላከለ መሆኑ፤ለምሳሌ፡-

☞ በ2014 ዓ.ም በ9 ወንድ እና በ2 ሴት ሰራተኞች ላይ አደጋ የደረሰ መሆኑ፤

➢ ፋብሪካው የአደጋ መከላከያ ትጥቆችና አልባሳትን በወቅቱ፤በተፈለገ ጊዜና በበቂ ሁኔታ ለሰራተኞች የማያቀርብ መሆኑ፤

ታውቋል፡፡

73.ስለጉዳዩ የፋብሪካው የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ፤በረቂቅ ሪፖርት እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት መልስ፡-

➢ ለፋብሪካው የአካባቢ አስተዳደር እና የጤናና ደኅንነት ስርዓት መዘርጋት እና ተግባራዊ ማድረግ ለድርጅቱ አስፈለጊ መሆናቸውን እና የአካባቢ አስተዳደር ስርዓትን (Environmental Management System) ISO 14001፡2015ን በተመለከተ የዶክመንት

ስራዎች የተዘጋጁ ቢሆንም የሚቀሩ የኮንስትራክሽን ስራዎች መኖራቸውን እና የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ እስካሁን ያልተጠናና ለወደፊት መጠናት እንዳለበት የሚያምኑ መሆኑን፤

- የምስክር ወረቀት ያላገኘነው በእስታንዳርዱ መሰረት መሰራት ያለበት ሥራ ስላልተሰራና በሥራ ላይ የሚደርሱ ጉዳቶችን ያልተከላከሉ በመሆኑ፤በ2014ዓ.ም የአደጋ መከላከያ አልባሳት ያልተገዛ መሆኑን አረጋግጠው ሰራተኞች የተሰጣቸውን አልባሳት በአግባቡ እንዲጠቀሙ የመቆጣጠር ስራ እንደሚሰሩ ገልፀዋል፡፡

74. ለፋብሪካው አስተዳደር እና ጤና ደህንነት ለመጠበቅ የሚያስችሉ ስርዓቶች ተገቢውን ትኩረት አለመስጠት በኦዲቱ እንደ ክፍተት ለተወሰደው በፋብሪካው የአካባቢ አስተዳደር (Environmental Management System) እና የጤናና ደኅንነት ስርዓትን (Occupational Safety and Health Management) በመዘርጋት ተግባራዊ ላለማድረጉ እንደምክንያትነት ሊጠቀስ ይችላል፡፡

75. ፋብሪካው የአካባቢ አስተዳደር ደህንነት ስርዓት (Environmental Management System) ባለመዘርጋቱ እና የጤናና ደኅንነት ስርዓትን (Occupational Safety and Health Management) ባለመተግበሩ በሥራ ላይ የሚደርሱ ጉዳቶችን እንዳይከላከል አድርጓል፤

## የፋብሪካው መጋዝን እና ደህንነት መሳሪያዎችን በተመለከተ፤

76. ፋብሪካው የምርት ግብዓቶችን፤ የተመረቱ የኬሚካል ምርቶችን ለማከማቸት የሚያስችል ጥራቱንና ደህንነቱን የጠበቀ መጋዘን፤የምርት አቀማመጥ ስርዓት ሊኖረው እና የአደጋ ጊዜ ጠቋሚ መሰሪያዎች (Smoke detector)፤ ተቀጣጣይ ዕቃዎችና የእሳት ማጥፊያዎች በተገቢውና በተዘጋጀላቸው ስፍራ በስርዓትና በጥንቃቄ መቀመጣቸውን ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

77. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-

- <u>ለፋብሪካው ምርት ግብዓቶች የሚሆኑ መጋዘኖችን በተመለከተ፤</u>

- ለአልሙኒየም ሰልፌት እና የሰልፈሪክ አሲድ ኬሚካል ግብዓቶች ማስቀመጫ የሚሆኑ መጋዘኖች ያሉ መሆኑ፤
- ለሃይድሮጅን ፐርኦክሳይድ ምርት የሚያገለግሉ ግብዓቶች ደረጃውን ባልጠበቀ የቆርቆሮ መጋዘን የሚገኙ መሆናቸው፡፡

DRAFT

☞ በተጨማሪ ለሃይድሮጅን ፐርኦክሳይድ ምርት የሚያገለግሉ እ.ኤ.አ 26/07/2016 ተገዝተው የገቡ ኬሚካሎች፡ ፓላዲሄም ካታሊስት (Palladium Catalyst) 50 ኪሎግራም፤አክትቬትድ አሉሚና (Activated Alumina) 15,400 ኪሎግራም እና Ethyl Antha Quinone 1,600 ኪሎግራም እንዲሁም እ.ኤ.አ 28/03/2022 ተገዝቶ የገቡ ኬሚካሎች ፓላዲሄም ካታሊስት (Palladium Catalyst) 25 ክሎግራም፤ አክትቬትድ አሉሚና (Activated Alumina) 12,000 ክሎግራም እና Ethyl Antha Quinone 875 ኪሎግራም ማለትም በጠቅላላ 29,950 ኪሎግራም የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈባቸው ኬሚካሎች /Expaired chemicals/ ጊዜያቸው ካላለፈባቸው ግብዓቶች ጋር ተቀላቅለው በመጋዘኑ ውስጥ ያለ አግባብ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፤



ስዕል 5፡ ጊዜያቸው ያለፈባቸው እና ያላለፈባቸው የኬሚካል ግብዓቶች ተቀላቅለው በቆርቆሮ መጋዘን ውስጥ ያለ አግባብ ስለመከማቸታቸው የሚያሳይ

- <u>የአደጋ ጊዜ ጠቋሚ መሣሪያዎችን በተመለከተ፤</u>

  - ፋብሪካው በሃይድሮጂን ፔርኦክሳይድ፣ በነባሮቹ የአሉሚኒየም ሰልፌት እና ሰልፈሪክ አሲድ ማምረቻ ዩኒቶች የፋየር አላርምና በአደጋ ጊዜ የድምፅ መስጪያ ሲስተም አቅርቦት፣ ዝርጋታ እና ተከላ ያልተደረገለት መሆኑ፣ ለምሳሌ፡-

☞ በፋብሪካው መለዋወጫ መጋዘንና የኤሌክትሪክ ሃይል ማሰራጫ ህንፃ ላይ የተገጠሙ የጢስ ጠቋሚዎች (Smoke detector) ለረጅም ጊዜ የማይሠሩ መሆኑ፣እንዲሁም አደገኛ ኬሚካሎች፤ተቀጣጣይ እቃዎችና የእሳት ማጥፊያዎች በተገቢውና በተዘጋጀላቸው ስፍራ በሥርዓት እና በጥንቃቄ ያልተቀመጡ መሆኑ፤

78.ስለጉዳዩ የፋብሪካው የበላይ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ መጠይቅ እና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ወቅት በሰጡት መልስ፡-

- የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈው ኬሚካሎች በሳተላይት /ቆርቆሮ/ መጋዘን ውስጥ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑን፤
- ፋብሪካው ለጥሬ ዕቃና ለምርት ማከማቻ የሚሆኑ ትላልቅ መጋዘኖች ያሉት ቢሆንም ለሃይድሮጅን ፐርኦክሳይድ ምርት ማከማቻ የሚሆን በቂ መጋዘን የሌለው መሆኑን፤
- ነበሮቹ ፋብሪካዎች የእሳት አደጋ ጠቋሚ መሳሪያዎች የነበራቸው ቢሆንም አሁን ላይ መስራት እንዳቆሙና ወደፊት እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ የሚሰሩ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

79.የምርት እና ግብዓት አቀማመጥ እና ደህንነት ስራዎች የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ባለመተግበሩ እንዲሁም የምርት ግብዓቶችን የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ሳያልፍ ባለመጠቀሙ በኦዲቱ እንደ ክፍተት ለተወሰደው የተመረቱ የኬሚካል ምርቶችን ለማከማቸት የሚያስችል ጥራቱንና ደህንነቱ የጠበቀ መጋዘን በበቂ ሁኔታ እንዳይኖር ለማድረጉ እንደምክንያትነት ሊጠቀስ ይችላል፡፡

80.ፋብሪካው የምርት ግብዓቶችንና የተመረቱ የኬሚካል ምርቶችን ለማከማቸት የሚያስችል ጥራቱንና ደህንነቱን የጠበቀ መጋዘን እና የግብዓትና የምርት አቀማመጥ ስርዓት ካልተበጀለት ለግብዓትና ምርት ብልሽት ሊያጋልጥ የሚችል ሲሆን የአደጋ ጊዜ ጠቋሚ መሳሪያዎች (Smoke detector)፤ ተቀጣጣይ ዕቃዎችና የእሳት ማጥፍያዎች በተገቢውና በተዘጋጀላቸው ስፍራ በስርዓትና በጥንቃቄ መቀመጣቸውን ባለመቆጣጠሩ ሊደርሱ የሚችሉ አደጋዎችን አስቀድሞ ለመገንዘብ እንዳይቻል እና የከፋ ጉዳት እንዲያደርስ ሊያደርግ ይችላል፡፡

**የፋብሪካው ምርት በሚጓጓዝበት ወቅት ስለሚያደርገው የደህንነት ጥንቃቄ፤**

81.ፋብሪካው ምርቶችን በሚያመርትበት፤በሚያጓጉዝበት ወቅት በሰው፣ በንብረት እና በአካባቢ ላይ አደጋ የማያስከትሉ መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

82.ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-

- ፋብሪካው የሚያመርታቸውን የኬሚካል ምርቶችን ለመጓጓዝ የሚጠቀማቸው ተሽከርካሪዎች ሽፍን (ኮንቴነር) ያልሆኑና የአደጋ ጊዜ የደኅንነት መጠበቂያ መሳሪያዎች ያልተሟሉላቸው መሆኑ፤
- ፋብሪካው ምርቶቹን በሚያጓጓዝበት ወቅት በሰው፣ በንብረት እና በአካባቢ ላይ አደጋ የማያስከትሉ መሆኑን የማያረጋግጥ መሆኑ፤

83. ስለጉዳዩ የፋብሪካው የበላይ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ መጠይቅ እና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ወቅት በሰጡት መልስ፡-

- ፋብሪካው ሲገነባ ሰልፈሪክ አሲድ በታንከር እንደሚጓጓዝ ታስበው የተገነባ ቢሆንም ተግባራዊ እንዳልሆነና አሁን ላይ ፋብሪካው ለምርት መጓጓዣነት የሚጠቀማቸው ተሽከሪካሪዎች ተሳቢ የጭነት ተሽከሪካሪዎች መሆናቸውን እና የተሰጠውን ምክረሃሳብ በመውስድ በቀጣይ እንደሚያስተካክሉ ገልጸዋል፡፡

84. ለሰልፈሪክ አሲድ ለማጓጓዝ ታስቦ የተገነባ ታንከር ተግባራዊ ባለመሆኑ እና አስፈላጊውን ጥንቃቄ ለመተግበር ባለመቻላቸው በኦዲቱ እንደ ክፍተት ለተወሰደው ፋብሪካው ምርቶችን በሚያመርትበት እና በሚያጓጉዝበት ወቅት በሰው፣ በንብረት እና በአካባቢ ላይ አደጋ ለማስከተል ስጋት እንዲፈጥር ለማድረጉ እንደምክንያት ሊጠቀስ ይችላል፡፡

85. ፋብሪካው ምርቶቹን በሚያጓጓዝበት ወቅት በሰው፣በንብረት እና በአካባቢ ላይ አደጋ የማያስከትሉ መሆኑን የማያረጋግጥ በመሆኑ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት አስቀድሞ ለመከላከል እንዳይችል ሊያደርግ ይችላል፡፡

# ክፍል ሦስት

## መደምደሚያ

86.ከላይ በኦዲት ግኝቶች ላይ እንደተመለከተው በኬሚካል እንዱስትሪ ኮርፖሬሽን የአዋሽ መልካሳ ኬሚካል ፋብሪካ የሥራ አፈጻጸም እና የአካባቢ አያያዝ ሥርዓት የታሰበውን ዓላማ ማሳካት የተቻለ መሆኑ ሲገመገም የሚከተሉት የአሠራር ግድፈቶች እና ክፍተቶች በመኖሩ የሚከተሉት መደምደሚያ ሃሳቦች ላይ ተደርሷል፡፡

- ☞ ፋብሪካው የፕሪፎርማ ግዥዎች የመንግስት ግዥ መመሪያን እና የኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን የግዥ መመሪያ ቁጥር 07/2012 ያልተከተሉ መሆኑ፤ እንዲሁም ለምርት አገልግሎት የሚውሉ የግብዓት ግዥዎችን ሲፈፅም ዝርዝር የግዥ ዕቅድ የሌለውና በተፈለገው ጊዜ፣መጠን፣ጥራት እና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ ያልተከናወኑ ናቸው፡፡
- ☞ ፋብሪካው የግብዓት ምርቶችን በአገር ውስጥ ለማምረት የአዋጭነት ጥናት በማስጠናት ከውጭ ሀገር የሚገቡትን ተመሳሳይ ምርቶች (ግብዓቶችን) በፋብሪካው የማያመርት በመሆኑ ለግብዓት እጥረትና ውል የተቋረጠባቸው ደንበኞች ጭምር ለከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ወጪ እየተዳረገ ነው፡፡
- ☞ ፋብሪካው በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ  የንብረት አስተዳደር ስርዓት በመዘርጋት የንብረት እንቅስቃሴን በአግባቡ ያልተከታተለ ሲሆን ፤አገልግሎት ሊሰጡ የማይችሉ ንብረቶችንና ተረፈምርቶችን የሚያስወግድበት ስርዓት ባለመዘርጋቱ በፋብሪካው ግቢ ውስጥ በየቦታው ተደፍተው የሚገኙ የካኦሊን ኬክ ተረፈ ምርቶች የግቢውን ገፅታ እያበላሹና ነፀብራቁ በሰው ዐይን ላይ ጉዳት እያደረሰ ይገኛል፡፡
- ☞ የፋብሪካው ነባር ፋብሪካዎችን መልሶ የማቋቋም እና የሃይድሮጅን ፐርኦክሳይድ ፋብሪካ የግንባታ ፕሮጀክቶች ኮንትራት ውሉ ላይ በተቀመጠው መስፈርት /Specification/ እና በውል ሰነዱ የጥራት ስታንዳርድ መሰረት በተያዘላቸው በጀት እና ጊዜ ተገንብተው ወደ ምርት ማምረት ሂደት አልገቡም፡፡በዚህም ምክንያት የሃይድሮጅን ፐርኦክሳይድ ፋብሪካ የግንባታ ፕሮጀክት ውል ከተገባው የ86,243,291.06 (የሰማኒያ ስድስት ሚሊዮን ሁለት መቶ አርባ ሦስት ሺህ ሁለት መቶ ዘጠና አንድ ብር ከስድስት ሳንቲም) ወይም 60.68% ጭማሪ ወጪ ተዳርጓል፡፡
- ☞ ፋብሪካው ግንባታው የተጠናቀቀውን የሃይድሮጅን ፐርኦክሳይድ ፋብሪካ የግንባታ ፕሮጀክት የመጨረሻ ርክክብ በውሉ መሰረት ተግባራዊ ያላደረገ እንዲሁም በታዩ

ግድፈቶች /Defects/ ላይ በወቅቱ ህጋዊ እርምጃ ያልወሰደ በመሆኑ ፕሮጀክቱ በውል መሠረት በጊዜ እና በተቀመጠላቸው ጥራት እንዳይጠናቀቅ እና የምርት ሂደቱ በታቀደው ልክ እንዳይሄድና እንዲስተጓጎል አድርጓል፡፡

☞ ፋብሪካው ውጤታማ የሆነ የጥገና (maintenance) ስርዓት በመዘርጋት አስፈላጊ የመለዋወጫ (የጥገና መሳሪያዎችን) በመያዝ የምርት ሂደቱ እንዳይስተጓጎል አላደረገም፡፡ በዚህም በመለዋወጫ እቃ እጥረት ምክንያት 82,194.94 የባከነ/ሥራ ላይ ያልዋለ/ ሰዓት (Down time) እንዲመዘገብ አድርጓል፡፡

☞ ፋብሪካው ለሚያመርታቸው የኬሚካል ምርቶች በየወቅቱ የደሰሳ ጥናት በማድረግ የገበያ መዳረሻዎችን (በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር) ያላሰፋ በመሆኑ ከገበያ ድርሻው ሊያገኝ የሚገባውን ገቢ እንዲያጣ አድርጓል፡፡

☞ ፋብሪካው ምርታማነቱን በማሳደግ የአልሙኒየም ሰልፌት፣ ሰልፈሪክ አሲድ እና ሃይድሮጅን ፔር ኦክሳይድ ኬሚካል ምርቶች በሶስት አመት (ከ2012-2014 ዓ.ም) ሊደርስበት ከሚችለው የማምረት አቅም (Attainable Design Capacity) ልክ (30,308 ቶን) ባለማምረቱ ብር 277,996,009.60 ማግኘት የነበረበትን ገቢ እንዲያጣ ንዲሁም ከተለያዩ ድርጅቶች ጋር የገባውን የኬሚካል ምርቶች አቅርቦት በገባው የውሉ ኮንትራት መሰረት በወቅቱ መፈፀም እንዳይችል አድርጓል ፋብሪካው ለሚያመርታቸው ምርቶች ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት የጥራት ማረጋገጫ በማግኘት የምርት ጥራት መረጃ በምርት ማሸጊያዎቹ ላይ እንዲለጠፍ አያደርግም፡፡ ይህም በ2017 ዓ.ም በምስራቅ አፍሪካ ካሉ ኬሚካል ፋብሪካዎች ግንባር ቀደም በመሆን ተወዳዳሪ ለመሆን ፋብሪካው ከያዘው ራዕይ አንፃር ሊያሳካ አይችልም፡፡

☞ ፋብሪካው የጀሪካን ማምረቻ ግንባታ ፋብሪካ ተግባራዊ በማድረግ ጥራታቸውና ደህንነታቸው የተጠበቀ የኬሚካል ምርት ማሸጊያ ጀሪካኖች በማምረት ምርቶቹን እንዲታሸጉ አላደረገም፡፡

☞ ፋብሪካው የአካባቢ አስተዳደር ስርዓትን በመዘርጋት የደረቅ እና የፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ እንዲሁም የአየር ብክለት መከላከል ስራዎችን በአግባቡ አልሰራም፤ የጤና እና ደህንነት ስርዓት በመዘርጋት ለሠራተኞቹ የአደጋ መከላከያ ትጥቆችና አልባሳትን በወቅቱና በተፈለገ ጊዜ በማቅረብ በሥራ ላይ የሚደርሱ ጉዳቶችን ለመከላከል የሚያስችል ደህንነቱ የተጠበቀ የሥራ አካባቢን አልፈጠረም፡፡

☞ ፋብሪካው የሃይድሮጅን ፔርኦክሳይድ የምርት ግብዓቶችንና የተመረቱ የኬሚካል ምርቶችን ለማከማቸት የሚጠቀመው መጋዘን ጥራቱንና ደህንነቱን ያልጠበቀ

የግብዓትና የምርት አቀማመጥ ስርዓት ያልተበጀለት፣ የአደጋ ጊዜ ጠቋሚ መሰሪያዎች (Smoke detector)፣ ተቀጣጣይ ዕቃዎችና የእሳት ማጥፍያዎች በተገቢውና በተዘጋጀላቸው ስፍራ በስርዓትና በጥንቃቄ ያልተቀመጡ ናቸው፡፡

☞ ፋብሪካው ምርቶቹን በሚያጓጓዝበት ወቅት በሰው፣ በንብረት እና በአካባቢ ላይ አደጋ የማያስከትሉ መሆናቸውን አያረጋግጥም፡፡

የሚሉ ናቸው፡፡

በመሆኑም በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን ድክመቶች እና ችግሮች ለማስወገድ ወይንም ለማቃለል አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል አቅርበናል፡፡

DRAFT

# ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሃሳቦች

87.የአዋሽ መልካሳ ኬሚካል ፋብሪካ የሥራ አፈጻጸም እና የአካባቢ አያያዝ ሥርዓትን ተከትለው እንዲተገበሩ ያስችላሉ ተብለው የታመነባቸው የማሻሻያ ሃሳቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- ☞ ፋብሪካው የፕሪፎርማ ግዥዎች የመንግስት ግዥ መመሪያን እና የኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን የግዥ መመሪያ ቁጥር 07/2012 የተከተሉ እንዲሆኑ እንዲሁም ለምርት አገልግሎት የሚውሉ የግብዓት ግዥዎችን ሲፈፅም ዝርዝር የግዥ ዕቅድ ሊያዘጋጅና በተፈለገው ጊዜ፣መጠን፣ጥራት እና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ ሊያከናውን ይገባል፡፡
- ☞ ፋብሪካው የግብዓት ምርቶችን በአገር ውስጥ ለማምረት የአዋጭነት ጥናት በማስጠናት ጥናቶቹን ተግባራዊ በማድረግ በሚመለከታቸው አካላት የፖሊሲ ድጋፍ እንዲያገኝ ጥረቶችን በማድረግ ተመሳሳይ ምርቶችን በፋብሪካው ማምረት አለበት፡፡ እንዲሁም

ከውጭ ለሚያስገባቸው ግብዓት ግዥ የሚያስፈልገውን የውጭ ምንዛሪ ዕጥረት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ጋር በመነጋገር በዘላቂነት በመፍታት የሚያመርታቸውን ኬሚካሎች ለደንበኞቹ በበቂ ሁኔታ ማቅረብ አለበት፡፡

☞ ፋብሪካው የተደራጀ የውስጥ አቅም በመገንባት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የንብረት አስተዳደር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ እና የንብረት እንቅስቃሴን በአግባቡ ሊከታተል እንዲሁም አገልግሎት ሊሰጡ የማይችሉ ንብረቶችንና ተረፈምርቶችን በአግባቡ ማስወገድ አለበት፡፡

☞ ፋብሪካው ያለበትን የመከታተል ሃላፊነት ትኩረት ሰጥቶ በመፈፀም ነባር ፋብሪካዎችን መልሶ የሚቋቋም  የግንባታ ፕሮጀክቶች ኮንትራት ውሉ ላይ በተቀመጠው መስፈርት /Specification/ እና በውል ሰነዱ የጥራት ስታንዳርድ መሰረት  በተያዘላቸው በጀት እና ጊዜ ገንብተው ወደ ምርት ማምረት ሂደት ማስገባት አለበት፤

☞ ፋብሪካው ወቅታዊ ምላሽ የሚያስፈልጋቸውን ጉዳዮች ለመወሰን እና የታዩ ግድፈቶን ህጋዊ እርምጃ ለመውሰድ በቁርጠኝነት በመስራት ግንባታው የተጠናቀቀው የሃይድሮጅን ፐርኦክሳይድ ፋብሪካ ፕሮጀክት የመጨረሻ ርክክብ በውሉ መሰረት ተግባራዊ በማድረግ፤በታዩ ግድፈቶች /Defects/ ላይ ሕጋዊ እርምጃ በመውሰድ ምርት ሂደቱ እንዳይስተጓጎል ማድረግ አለበት፡፡

☞ ፋብሪካው ውጤታማ የሆነ የጥገና (maintenance) ስርዓት በመዘረጋትና አስፈላጊ የመለዋወጫ (የጥገና መሳሪያዎችን) በመያዝ የምርት ሂደቱ እንዳይስተጓጎል ሊያደርግ ይገባል፡፡

☞ ፋብሪካው የገበያ መዳረሻ ጥናት ለምርት ሽያጭ አፈፃፀም ያለውን አስተዋፅኦ በአግባቡ በመረዳት እና ለሚያመርታቸው የኬሚካል ምርቶች በየወቅቱ የደሰሳ ጥናት በማድረግ የገበያ መዳረሻዎችን (በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር) ሊያሰፋና ከገበያ ድርሻው ሊያገኝ የሚገባውን ገቢ ሊያሳድግ ይገባል፡፡

☞ ፋብሪካው የፋብሪካው መሳሪያዎች ቴክኒካል ችግሮች በአስቸኳይ እንዲፈቱ በማድረግ እና ዘመናዊ የማምረት አሰራሮችን በመተግበር ሊደርስበት ከሚችለው የማምረት አቅም (Attainable Design Capacity) ልክ በማምረት ምርታማነቱን ሊያሳድግ እና ከተለያዩ ድርጅቶች ጋር የሚገባውን የኬሚካል ምርቶች አቅርቦት በሚገባው የውሉ ኮንትራት መሰረት በወቅቱ መፈፀም አለበት፡፡

☞ ፋብሪካው የጀሪካን ማምረቻ ግንባታ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል በጀት በመመደብ/ የሚመለከታቸው አካላት በጀት እንዲመድቡ የተለያዩ ጥረቶችን በማድረግ


እና የፋብሪካውን ግንባታ እንዲከናወን በማድረግ ለምርት ማሽኒያው ጥራታቸውና ደኅንነታቸው የተጠበቀ የኬሚካል ምርት ማሽኒያ ጀሪካኖች መጠቀም አለበት፡፡

- ☞ ፋብሪካው ለአካባቢ አስተዳደር እና ጤና ደህንነት ለመጠበቅ የሚያስችሉ ስርዓቶች ተገቢውን ትኩረት በመስጠት የአካባቢ አስተዳደር ስርዓትን በመዘርጋት የደረቅ እና የፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ እንዲሁም የአየር ብክለት መከላከል ስራዎችን በአግባቡ ሊሰራ በተጨማሪም የጤና እና ደህንነት ስርዓት በመዘርጋት ለሠራተኞቹ የአደጋ መከላከያ ትጥቆችና አልባሳትን በወቅቱና በተፈለገ ጊዜ በማቅረብ በሥራ ላይ የሚደርሱ ጉዳቶችን ለመከላከል የሚያስችል ደህንነቱ የተጠበቀ የሥራ አካባቢን መፍጠር አለበት፡፡
- ☞ ፋብሪካው የምርት እና ግብዓት አቀማመጥ እና ደህንነት ስራዎች የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት የምርት ግብዓቶችንና የተመረቱ ሁሉም የኬሚካል ምርቶችን ለማከማቸት የሚያስችል ጥራቱንና ደህንነቱን የጠበቀ መጋዘን እንዲኖረው በማድረግ ፤ አደጋ ጊዜ ጠቋሚ መሰሪያዎች (Smoke detector)፣ ተቀጣጣይ ዕቃዎችና የእሳት ማጥፍያዎች በተገቢውና በተዘጋጀላቸው ስፍራ በስርዓትና በጥንቃቄ እንዲቀመጡ እና በግብዓትና ምርት አቀማመጥ ችግር ምክንያት በአካባቢው ላይ ጉዳት እንዳያደርስ አስቀድሞ መከላከልና መቆጣጠር አለበት፡፡
- ☞ ፋብሪካው አስፈላጊውን ጥንቃቄ በመተግበር ምርቶቹን በሚያጓጓዝበት ወቅት በሰው፣ በንብረት እና በአካባቢ ላይ አደጋ የማያስከትሉ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት በአዋሽ መልካሳ ኬሚካል ፋብሪካ የበላይ ሥራ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች እንዲሁም መረጃ የሰበሰብንባቸው የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት የስራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ለኦዲቱ ሥራ መሳካት ላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

አባሪ- አንድ

## የአዋሽ መልካሳ ኬሚካል ፋብሪካ ድርጅታዊ መዋቅር




DRAFT

## የመመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria)

**የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት፡ በኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን የአዋሽ መልካሳ ኬሚካል ፋብሪካ**

**የኦዲቱ አካባቢ፡ የአዋሽ መልካሳ ኬሚካል ፋብሪካ የሥራዎች አፈፃፀም እና የአካባቢ አያያዝ ሥርዓት ውጤታማነትን መገምገም፡፡**

| ተ/ቁ | የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች(Audit Issues) | የመመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria) |
|---|---|---|
| 1 | በፋብሪካው የሚከናወኑ ግዥዎች የመንግስት ግዥ ሕጎችን የተከተሉና የንብረት አሰተዳደር ስርዓት ውጤታማ መሆኑን መገምገም | 1. ፋብሪካው መልሶ የሚያቋቁማቸው እና የሚያስገነባቸው የኬሚካል ፋብሪካ ፕሮጀክቶች አለም አቀፍ የግዥ ሕጎችንና የመንግስት ግዥ ህግና መመሪያ ሂደትን የተከተለ ሊሆኑ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡- የኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን የግዥ መመሪያ ቁጥር 07/2002 |
| | | 2. ፋብሪካው ለምርት አገልግሎት የሚውሉ የግብዓት ግዥዎችን ሲፈፅም በዕቅድ ሊመራና በተፈለገው ጊዜ፣ መጠን፣ ጥራት እና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ ሊፈጽም ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡- የኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን የግዥ መመሪያ ቁጥር 07/2002 |
| | | 3. ፋብሪካው የተጫራቾቹን የቴክኒካል እና ፋይናንሻል ብቃት (Qualification) በማረጋገጥ በቅድመ ጨረታ ሂደት ውስጥ አልፈው የሚመጡ ተጫራቾች ውል በሚፈፀምበት ጊዜ አስተማማኝ የብቃት ደረጃ ላይ የሚገኙ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ድህረ ብቃት ግምገማ ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡- የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ/2002 ዓ.ም |
| | | 4. ፋብሪካው የመንግስት ንብረት አያያዝ መመሪያን በመከተል የንብረት አስተዳደር ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡- የንብረት አያያዝ መመሪያ 2002 |
| | | 5. ፋብሪካው አገልግሎት ሊሰጡ የማይችሉ ንብረቶችንና ተረፈምርቶችን አወጋገድ ስርዓት ሊኖረውና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡- የንብረት አያያዝ መመሪያ 2002 |

DRAFT

| ተ/ቁ | የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች(Audit Issues) | የመመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria) |
|---|---|---|
| 2 | በፋብሪካው የሚከናወኑ ግንባታዎች የኮንትራት ውል አስተዳደር ውጤታማነትን መገምገም፡፡ | 6. የፋብሪካው የግንባታ ፕሮጀክቶች በገቡት ውል መሰረት ስለመፈጸማቸው ለመከታተል የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋና አስፈላጊውን የእርምት እርምጃ በወቅቱ ሊወስድ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡-የሃይድሮጅን ፐርኦክሳይድ እና የነባር ፋብሪካ መልሶ ማቋቋም የኮንትራት ውል ቁጥር 8720 ቀን 02/01/2012 እና የኮንትራት ውል ቁጥር 9570 ቀን 13/12/2021 |
| | | 7. ፋብሪካው ነባር ፋብሪካዎችን መልሶ የሚቋቋም እና የሃይድሮጅን ፐርኦክሳይድ ፋብሪካ የግንባታ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ጊዜ እና በጀት ሊጠናቀቁ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡- የሃይድሮጅን ፐርኦክሳይድ እና የነባር ፋብሪካ መልሶ ማቋቋም የኮንትራት ውል ቁጥር 8720 ቀን 02/01/2012፣ የኮንትራት ውል ቁጥር 9570 ቀን 13/12/2021 |
| | | 8. ፋብሪካው ነባር ፋብሪካዎችን መልሶ የሚቋቋም እና የሃይድሮጅን ፐርኦክሳይድ ፋብሪካ የግንባታ ፕሮጀክቶች ኮንትራት ውሉ ላይ በተቀመጠው መስፈርት /Specification/ እና በውል ሰነዱ የጥራት ስታንዳርድ መሰረት ተገንብተው ወደ ምርት ማምረት ሂደት ሊገቡ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡- የሃይድሮጅን ፐርኦክሳይድ እና የነባር ፋብሪካ መልሶ ማቋቋም የኮንትራት ውል ቁጥር 8720 ቀን 02/01/2012፣ የኮንትራት ውል ቁጥር 9570 ቀን 13/12/2021 |
| | | 9. ፋብሪካው ግንባታቸው የተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች የመጨረሻ ርክክብ በውሉ መሰረት ተግባራዊ በማድረግ የታዩ ግድፈቶች /Defects/ ካሉ ህጋዊ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡-የሃይድሮጅን ፐርኦክሳይድ እና የነባር ፋብሪካ መልሶ ማቋቋም የኮንትራት ውል ቁጥር 8720 ቀን 02/01/2012፣ የኮንትራት ውል ቁጥር 9570 ቀን 13/12/2021 |
| | | 10. ፋብሪካው ውጤታማ የሆነ የጥገና (maintenance) ስርዓት በመዘረጋት አስፈላጊ የመለዋወጫ (የጥገና መሳሪያዎችን) በመያዝ የምርት ሂደቱ እንዳይስተጓጎል ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡-የሃይድሮጅን ፐርኦክሳይድ እና የነባር ፋብሪካ መልሶ ማቋቋም የኮንትራት ውል ቁጥር 8720 ቀን 02/01/2012፣ የኮንትራት ውል ቁጥር 9570 ቀን 13/12/2021 |

DRAFT


| ተ/ቁ | የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች(Audit Issues) | የመመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria) |
|---|---|---|
| 3 | የፋብሪካው የምርትና የማምረት ብቃት (Operation and Process Efficiency) ሂደትን መገምገም | 11. ፋብሪካው ዓለም አቀፍ የጥራት ደረጃቸውን ያሟሉ አሉሚኒየም ሰልፌት፣ ሰልፈሪክ አሲድ እና ሃይድሮጅን ፐርኦክሳይድ ኬሚካሎችን ዘመናዊ የአመራረት ቴክኖሎጂን በመጠቀም በማምረት አቅሙ (Design Capacity) ልክ ሊያመርት ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡- የሃይድሮጅን ፐርኦክሳይድ እና የነባር ፋብሪካ መልሶ ማቋቋም የኮንትራት ውል ቁጥር 8720 ቀን 02/01/2012፣ የኮንትራት ውል ቁጥር 9570 ቀን 13/12/2021 |
| | | 12. ፋብሪካው የጥራት ማኔጅመንት ስርዓት (Quality Management System) በመዘርጋት የምርት ጥራት ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡- ስትራቴጂክ እቅድ 2013-2017 |
| | | 13. ፋብሪካው ምርታማነቱን በማሳደግ ከተለያዩ ድርጅቶች ጋር የገባውን የኬሚካል ምርቶች አቅርቦት በገባው የውሉ ኮንትራት መሰረት በወቅቱ ሊፈጽም ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡- የሽያጭ ውል ስምምነት |
| | | 14. ፋብሪካው ከውጭ ሀገር የሚገቡትን ተመሳሳይ ምርቶች (ግብዓቶችን) በፋብሪካው ሊያመርት ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡- ስትራቴጂክ እቅድ 2013-2017 |
| | | 15. ፋብሪካው ለሚያመርታቸው የኬሚካል ምርቶች በየወቅቱ ደሰሳ ጥናት በማድረግ የገበያ መዳረሻዎችን (በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር) በማስፋት የገበያ ድርሻውን ሊያሳድግ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡- ስትራቴጂክ እቅድ 2013-2017 |
| 4 | የአዋሽ መልካሳ ኬሚካል ፋብሪካ የአካባቢ አያያዝ ስርዓት ውጤታማነትን መገምገም፡፡ | 16. ፋብሪካው የአካባቢ አስተዳደር ደህንነት ስርዓት (Environmental Management System) በመዘርጋት የደረቅ ቆሻሻ፣ የፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ እና የአየር ብክለት መከላከል ስራዎችን ሊሰራ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡- ከሙያ ደህንነት፣ጤንነትና አካባቢ ጥበቃ መምሪያ ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት 2012-2014 ዓ.ም |
| | | 17. ፋብሪካው የጤናና ደህንነት ስርዓትን (Occupational Safety and Health Management) በመተግበር በሥራ ላይ የሚደርሱ ጉዳቶችን በመከላከል ለሠራተኞቹ ደህንነቱ የተጠበቀ የሥራ አካባቢን በመፍጠር የአደጋ መከላከያ ትጥቆችና አልባሳትን በወቅቱና በተፈለገ ግዜ |

| ተ/ቁ | የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች(Audit Issues) | የመመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria) |
|---|---|---|
| | | ሊያቀርብ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡- ከሙያ ደህንነት፤ጤንነትና አካባቢ ጥበቃ መምሪያ ዕቅድ አፋፃፀም ሪፖርት 2012-2014 ዓ.ም |
| | | 18. ፋብሪካው የተጠናውን የጀሪካን ፋብሪካ በመገንባት ጥራታቸውና ደህንነታቸው የተጠበቀ የኬሚካል ምርት ማሸጊያ ጀሪካኖች ሊያመርት ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡- ስትራቴጂክ እቅድ 2013-2017 |
| | | 19. ፋብሪካው የምርት ግብዓቶችንና የተመረቱ የኬሚካል ምርቶችን ለማከማቸት የሚያስችል ጥራቱንና ደህንነቱን የጠበቀ መጋዘን እና የግብዓትና የምርት አቀማመጥ ስርዓት ሊኖረው ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡-የኢንዱስትሪ ኬሚካሎች ምዝገባና አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1075/2010 ዓ.ም |
| | | 20. ፋብሪካው ምርቶችን በሚያመርትበት፤በሚያጓጉዝበት ወቅት በሰው፣ በንብረት እና በአካባቢ ላይ አደጋ የማያስከትሉ መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡-የኢንዱስትሪ ኬሚካሎች ምዝገባና አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1075/2010 ዓ.ም |
| | | 21. ፋብሪካው አደገኛ ኬሚካሎች የአደጋ ጊዜ ጠቋሚ መሰሪያዎች (Smoke detector) ፤ተቀጣጣይ ዕቃዎችና የእሳት ማጥፍያዎች በተገቢውና በተዘጋጀላቸው ስፍራ በስርዓትና በጥንቃቄ መቀመጣቸውን ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡-ከሙያ ደህንነት፤ ጤንነትና አካባቢ ጥበቃ መምሪያ ዕቅድ አፋፃፀም ሪፖርት 2012-2014 ዓ.ም |

DRAFT

አባሪ- ሶስት

## የአዋሽ መልካሳ ኬሚካል ፋብሪካ የአሰራር ስርዓት መግለጫ



## አባሪ- አራት

**ፋብሪካው የሚፈለገው ምርት ስለመገኘቱ፤**

- ፋብሪካው አሉሚኒየም ሰልፌት፣ሰልፈሪክ አሲድ እና ሃይድሮጅን ፐርኦክሳይድ ኬሚካሎችን ዘመናዊ የአመራረት ቴክኖሎጂን በመጠቀም ሊደርስበት ከምችለው የማምረት አቅም (Attainable Design Capacity) ልክ የማያመርትና የማይሸጥ መሆኑ፤ለማሳያነት፡-

**<u>የ2012 በጀት ዓመት ምርትን በተመለከተ</u>**

- 7000 ቶን አሉሚኒየም ሰልፌት በብር 52,698,000 ለማምረት ታቅዶ በመጠን 2022 ቶን፣ በገንዘብ 20,078,000 አሉሚኒየም ሰልፌት በማምረት የዕቅዱን በመጠን 28.9%፣ በገንዘብ 38.1% ያከናወነ መሆኑ፣
- 6320 ቶን ሰልፈሪክ አሲድ በብር 47,500,000 ለማምረት ታቅዶ በመጠን 3088 ቶን፣ በገንዘብ 30,663,000 ሰልፈሪክ አሲድ በማምረት የዕቅዱን በመጠን 48.9%፣ በገንዘብ 64.6% ያከናወነ መሆኑ፣
- 2,300 ቶን ሃይደሮጂን ፔርኦክሳይድ በብር 24,125,000 ለማምረት ታቅዶ በመጠን 1032 ቶን፣በገንዘብ 10,248,000 ሃይድሮጂን ፔርኦክሳይድ በማምረት የዕቅዱን በመጠን 44.9%፣ በገንዘብ 42.5% ያከናወነ መሆኑ፤
- በአጠቃላይ በ2012 በጀት ዓመት 15,620 ቶን ምርት በብር 124,323,000 ለማምረት ታቅዶ በመጠን 7,132ቶን፣ በገንዘብ 60,989,000 ምርት በማምረት የዕቅዱን በመጠን 45.65%፣በገንዘብ 49.1% ያከናወነ መሆኑ፤

**<u>የ2012 በጀት ዓመት ሽያጭን በተመለከተ</u>**

- 5200ቶን አሉሙኒየም ሰልፌት በብር 71,204,000 ለመሸጥ ታቅዶ 2486.250 ቶን አሉሙኒየም ሰልፌት በብር 46,916,000 በመሸጥ የዕቅዱን በመጠን 47.81% እና በዋጋ 65.89% ያከናወነ መሆኑ፣
- 2500 ቶን ሰልፈሪክ አሲድ በብር 41,095,000 ለመሸጥ ታቅዶ 2,037.85 ቶን ሰልፈሪክ አሲድ በብር 32,525,000 በመሸጥ የዕቅዱን በመጠን 81.51%፤ በዋጋ 79.15% ያከናወነ መሆኑ፣

- 2308 ቶን ሃይድሮጂን ፔርኦክሳይድ በብር 49,874,000 ለመሸጥ ታቅዶ 583.69ቶን ሃይድሮጂን ፔርኦክሳይድ በብር 10,853,000 በመሸጥ የዕቅዱን በመጠን 25.29%፤በዋጋ 21.76% ያከናወነ መሆኑ፣
- በጠቅላላው በ2012ዓ.ም በጀት ዓመት 10,008 ቶን ምርት በብር 162,173,000 ለመሸጥ ታቅዶ 5,107.79 ቶን ምርት በብር 90,294,000 በመተሸጥ የዕቅዱን በመጠን 51.04% እና በዋጋ 55.68% ያከናወነ መሆኑ፤

**የ2013 በጀት ዓመት ምርትን በተመለከተ**

- 5,200 ቶን አሉሚኒየም ሰልፌት በብር 48,728,000 ለማምረት ታቅዶ በመጠን 3,288ቶን፣ በገንዘብ 41,601,000 አሉሚኒየም ሰልፌት በማምረት የዕቅዱን በመጠን 63.2%፣ በገንዘብ 85.4% ያከናወነ መሆኑ፣
- 5,123 ቶን ሰልፈሪክ አሲድ በብር 38,349,000 ለማምረት ታቅዶ በመጠን 3692.56ቶን፣ በገንዘብ 46,719,000 ሰልፈሪክ አሲድ በማምረት የዕቅዱን በመጠን 72.1%፣ በገንዘብ 121.8% ያከናወነ መሆኑ፣
- 2,167ቶን ሃይደሮጂን ፔርኦክሳይድ በብር 40,263,000 ለማምረት ታቅዶ በመጠን 282.39ቶን፣ በገንዘብ 3,573,000 ሃይድሮጂን ፔርኦክሳይድ በማምረት የዕቅዱን በመጠን 13.0%፣ በገንዘብ 8.9% ያከናወነ መሆኑ፤
- በአጠቃላይ 12,490ቶን ምርት በብር 127,340,000 ለማምረት ታቅዶ በመጠን 7,262.95 ቶን፣ በገንዘብ 91,353,000 ምርት በማምረት የዕቅዱን በመጠን 58.2%፣ በገንዘብ 71.73% ያከናወነ መሆኑ፡፡

**የ2013 በጀት ዓመት ሽያጭን በተመለከተ**

- 5200 ቶን አሉሙኒየም ሰልፌት በብር 73,232,000 ለመሸጥ ታቅዶ 3,192.1 ቶን አሉሙኒየም ሰልፌት በብር 87,589,000 በመሸጥ የዕቅዱን በመጠን 61.39%፤በዋጋ 119.6% ያከናወነ መሆኑ፣ በዋጋ ስታይ ከፍ ያለበት ምክንያት ድርጅቱ በምርቶቹ ላይ የመሸጫ ዋጋ ጭማሪ በማድረጉ የመጣ እንጂ ከዕቅድ በላይ የተሰራ ስራ የሌለ መሆኑ፤
- 2263 ቶን ሰልፈሪክ አሲድ በብር 37,687,000 ለመሸጥ ታቅዶ 2,045.2 ቶን ሰልፈሪክ አሲድ በብር 34,199,000 በመሸጥ የዕቅዱን በመጠን 90.37% ፤በዋጋ 90.74% ያከናወነ መሆኑ፣
- 2167 ቶን ሃይድሮጂን ፔርኦክሳይድ በብር 52,690,000 ለመሸጥ ታቅዶ 237.87 ቶን ሃይድሮጂን ፔርኦክሳይድ በብር 8,665,000 በመሸጥ የዕቅዱን በመጠን 10.98% ፤ በዋጋ 16.44% ያከናወነ መሆኑ፣

- በጠቅላላው 9630 ቶን ምርት በብር 163,609,000 ለመሸጥ ታቅዶ 5,475.17 ቶን ምርት በብር 130,453,000 በመሸጥ የዕቅዱን በመጠን 56.85%፤ በዋጋ 79.73% ያከናወነ መሆኑ፤

<u>የ2014 በጀት ዓመት ምርትን በተመለከተ</u>

- 6,713 ቶን አሉሚኒየም ሰልፌት በብር 54,430,495 ለማምረት ታቅዶ በመጠን 584 ቶን፣ በገንዘብ 14,965,013.86 አሉሚኒየም ሰልፌት በማምረት የዕቅዱን በመጠን 8.7%፣ በገንዘብ 27.5% ያከናወነ መሆኑ፣
- 6,638 ቶን ሰልፈሪክ አሲድ በብር 40,303,432 ለማምረት ታቅዶ በመጠን 187.4 ቶን፣ በገንዘብ 11,689,831.34 ሰልፈሪክ አሲድ በማምረት የዕቅዱን በመጠን 2.82%፣በገንዘብ 29% ያከናወነ መሆኑ፣
- 1,465 ቶን ሃይደሮጂን ፔርኦክሳይድ በብር 24,078,149 ለማምረት ታቅዶ በመጠን 252.75 ቶን፣ በገንዘብ 17,668,383 ሃይድሮጂን ፔርኦክሳይድ በማምረት የዕቅዱን በመጠን 17.25%፣ በገንዘብ 73.4% ያከናወነ መሆኑ፤
- በአጠቃላይ 14,816 ቶን ምርት በብር 118,812,076 ለማምረት ታቅዶ በመጠን 1,024.15 ቶን፣ በገንዘብ 44,323,228.20 ምርት በማምረት የዕቅዱን በመጠን 6.9%፣ በገንዘብ 37.31% ያከናወነ መሆኑ፤

<u>የ2014 በጀት ዓመት ሽያጭን በተመለከተ</u>

- 6,713 ቶን አሉሙኒየም ሰልፌት በብር 138,135,500 ለመሸጥ ታቅዶ 916 ቶን አሉሙኒየም ሰልፌት በብር 28,901,552.95 በመሸጥ የዕቅዱን በመጠን 21.7%፤ በዋጋ 20.9% ያከናወነ መሆኑ፣
- 2,402 ቶን ሰልፈሪክ አሲድ በብር 42,325,075 ለመሸጥ ታቅዶ 759.322 ቶን ሰልፈሪክ አሲድ በብር 15,977,569.45 በመሸጥ የዕቅዱን በመጠን 31.61% ፤ በዋጋ 37.75 % ያከናወነ መሆኑ፣
- 1,555 ቶን ሃይድሮጂን ፔርኦክሳይድ በብር 57,089,545 ለመሸጥ ታቅዶ 337 ቶን ሃይድሮጂን ፔርኦክሳይድ በብር 19,709,988 በመሸጥ የዕቅዱን በመጠን 21.69 % ፤ በዋጋ 34.52 % ያከናወነ መሆኑ፣
- በአጠቅላይ 10,670 ቶን ምርት በብር 237,550,120 ለመሸጥ ታቅዶ 2,012.322 ቶን ምርት በብር 64,589,110.40 በመሸጥ የዕቅዱን በመጠን 18.86 % ፤ በዋጋ 27.2 % ያከናወነ መሆኑ፤

**የፋብሪካው የሦስት ዓመታት ምርትን በተመለከተ**

በአጠቃላይ ፋብሪካው ከ2012 እስከ 2014 በጀት ዓመታት ባለው ጊዜ 42,926ቶን ምርትን ለማምርት፡-ማለትም አሉሙኒየም ሰልፌት በመጠን 18,913 ቶን ፣ሰልፈሪክ አሲድ በመጠን 18,081 ቶን እና ሃይድሮጂን ፔርኦክሳይድ በመጠን 5,932 ቶን ኬሚካል ምርቶችን በብር 370,475,076 ለማምርት ያቀደ ቢሆንም ፋብሪካው ማምረት ያቻለው በመጠን 14,429.1ቶን ማለትም አሉሙኒየም ሰልፌት 5,894 ቶን በብር 81,644,013.86፣ ሰልፈሪክ አሲድ 6,967.96 ቶን በብር 89,071,831.34 እና ሃይድሮጂን ፔርኦክሳይድ 1,567.14ቶን በብር 31,489,383 በማምረት በገንዘብ 202,205,228.20፤ የዕቅዱን በመጠን 33.61%፤በዋጋ 54.58%ያከናወነ መሆኑ፤ነገር ግን ከዕቅድ አንፃር 28,496.9 ቶን ምረት ማምረት የነበረበትን ምርት ያላመረተ መሆኑ፤

DRAFT